

የጉፋ ቅዱስ ገብርኤል ዕደ ጥበብ ማሠልጠኛ ት/ቤት ሥራውን የሚያከናውነው በዚህ መልክ ነው።

# ትንሣኤ



ተራዳኢው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል

ቁጥር [illegible]

[illegible] ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »


አዘጋጅ
ልሳነወርቅ በዛብህ ፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


## ማውጫ

### አርእስት ፤ — ገጽ


ደብዳቤዎች . . . . . . . . . . ፩
አንድነት ኃይል ነው . . . . . . . . ፪
የአርባ ቀን ጉዞ በአርባ ዓመት . . . . . ፬
ተራዳኢው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል . . . . ፭
ክርስቲያኖች የትንሣኤን በዓል ለምን በአንድ ቀን አያከብሩም ፰
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ይዞታ ፱
ልማት በቤተ ክርስቲያን . . . . . . ፲፪
ሐዋርያዊ ትእዛዝ . . . . . . . . ፲፬
የግብርና በረከት . . . . . . . . ፲፭
የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት . . . . . ፲፮
ፍቅር . . . . . . . . . . ፲፱
ዜና ሊቃውንት . . . . . . . . ፳፩
ትምህርተ ግዕዝ . . . . . . . . ፳፪
በጅማ ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት ከፍተኛ ስብሰባ ተደርጓል ፳፫


# ( ደ ብ ዳ ቤ ዎ ች )

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ ።
አዲስ አበባ ፤

በቅድሚያ ሥራችሁ የተቃና እንዲሆን እመኛለሁ ። ከዚህ ቀጥሎ ያልገቡኝ ጥቅሶች ስላሉ እነሱን እንድታብራሩልኝ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርባለሁ ።

፩ኛ/ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወንድ በ፵ ቀን ሴት በ፹ ቀን ክርስትና የሚነሡት ከምን የተገኘ ነው ?

፪ኛ/ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፥ ቁጥር ፴፬—፴፭ ያለው ቃል ስላልገባኝ ምሥጢሩ ምን እንደሆነ እንድታስረዱኝ በምድር ሰላምን ለማምጣት አይደለም ወይ ክርስቶስ የመጣው ?

፫ኛ/ በማቴዎስ ወንጌል ምዕ/ ፲፭፥ ቁ- ፳፮—፳፯ ላይ እንዲህ ይላል « እርሱ ግን መልሶ የልጆችን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም አለ እርስዋም አዎን ጌታ ሆይ ቡችሎችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ አለችው ይላል አባባሉ ስላልገባኝ እንድታስረዱኝ በቡችሎች የተመሰለ ማነው ?

ጠያቂ ገብረ መድኅን ገብሩ ከመንፈሳውያን ወጣቶች ማኅበር ደብረ ቤቴል ደብረ ግዕዛን መድኃኔ ዓለም አሥመራ ፤

— ወጣት ገ/ መድኅን ገብሩ በቅድሚያ ስላቀረብከው ጥያቄ እናመሰግንሃለን ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የጠየቅሃቸውን ጥያቄዎች እንመልሳለን ።

፩ኛ/ ጥያቄ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርርቲያን ወንዱን በ፵ ቀን ሴቲቱን በ፹ ቀን የምታጠምቅበት ምክንያት ሁለት መንገዶች አሉት ይኸውም ፩ኛ በኦሪት ዘሌዋውያን ም/ ፲፪፥፩- ፍጻሜ ድረስ ብታነበው እንዲህ የሚሉ ቃላትን ታገኛለህ፤ ሴት ብታረግዝና ወንድ ልጅንም ብትወልድ ፯ ቀን ያህል አትንጻም ከደምዋም እስክትነጻ ፴፫ ቀን ትቀመጥ የተቀደሰውንም ነገር አትንካ ወደ ቤተ እግዚአብሔር አትግባ ይላል እንግዲህ ፯ ቀንና ፴፫ ቀን ሲደመር ፵ ቀን ይሆናል ዘሌዋ ፲፪ ፣ ፪—፭ ፤

እንዲሁም ሴት ብታረግዝና ሴት ልጅንም ብትወልድ እንደ መርገምዋ ሕመም ለሁለት ሳምንት ያህል ከደም አትነጻም ከደምዋም እስክትነጻ ድረስ ፷፮ ቀን ትቀመጥ የተቀደሰውንም ነገር አትንካ ዘሌዋ ፲፪ ፣ ፭- ፮ ፪ ሳምንት የሚባለው ፲፬ ቀን ነው ፲፬ ቀንና ፷፮ ቀን ሲደመር ፹ ቀን ይሆናል የመንጻትም ወራት በተፈጸመ ጊዜ ለወንድ ልጅ ለሴትም ልጅ የአንድ ዓመት ጠቦት ለሚቃጠል መሥዋዕት ለኃጢአት ማስተስረያ ወደ ካህኑ ታመጣለች ። እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ያቀርባል ይላል ። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት በማድረግ ወንድ በ፵ ቀን ሴት በ፹ ቀን እንዲጠመቁ ኦርቶዶክሳዊት ቤት ክርስቲያን ወስናለች ። ፪ኛ/ ደግሞ በመጽሐፈ ኩፋሌ « በመጀመሪያይቱ ሱባኤ አዳም ተፈጠረ በሁለተኛይቱም ሱባኤ ሄዋንን ፈጥሮ አሳየው ስለዚህ በወሊድ ጊዜ ወንድ ልጅ ሰባት ቀን እንዲጠበቅ ሴት ልጅም ሁለት ሱባኤ እንድትጠበቅ ሥርዓት ተሠራ ካለ በኋላ በተፈጠረባት ምድር ለአዳም ፵ ቀን ከተፈጸመለት በኋላ ይገዛትም ይጠብቃትም ዘንድ ወደ ገነት አስገባነው ሚስቱ ሄዋንንም ፹ ቀን አስገባናት» ይላል ኩፋሌ ፬-፭-፱

ስለዚህ አዳም በተፈጠረ በ፵ ቀኑ ሄዋንም በተፈጠረች በ፹ ቀንዋ ወደ ገነት መግባታቸውን ምሳሌ በማድረግ ኦርቶዶካክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ወንድ ልጅ በተወለደ በ፵ ቀን ሴት ልጅም በተወለደች በ፹ ቀን እንዲጠመቁ የወሰነችበት ምክንያት ከዚህ የተነሳ ነው ።

፪ኛ/ ጥያቄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው የሰውን ኃጢአት ለማስተስረይና ፍጹም ነፃነቱን ለማጐናጸፍ ሲሆን ይኸውም ሰውን ምን ያህል እንደሚወደው የሚገልጽ ተግባር ነው እንዲያውም ወንጌላዊው ዮሐንስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍቅር እንጂ ለጠብ እንዳልመጣ ሲገልጽ « በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታልና በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና ዮሐ ፫ ፣ ፲፮ ፣ ፲፯ ።

እንግዲህ ማቴዎስ በ፲ ፣ ፴፬ ላይ በምድር ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይመስላችሁ ሰይፍን እንጂ ሲል የተናገረበት ምክንያት አለው ይኸውም ተስፋ ትንቢት የተነገረላቸው ሱባኤ የተቈጠረላቸው እስራኤላውያን ነበሩ ። ነገር ግን በተነገረው ተስፋ ትንቢትና በተቈጠረው ሱባኤ መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ገሚሶቹ በደስታ ሲቀበሉት እኩሌቶቹ ግን ፈጽመው አልተቀበሉትም ይህንንም ሲገልጽ ዮሐንስ « የገዛ ወገኖቹ አልተቀበሉትም ለተቀበሉት ግን የእግዚአብሔር ልጆች ይባሉ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው » ብሏል ዮሐ ፩ ፣ ፲፪ —፲፫ ።

አሁንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ላይ ሰላምን ለማምጣት የ...

ተከታዩ ወደ[illegible] ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

( ር እ ሰ   አ ን ቀ ጽ )

# እንድነት ኃይል ነው

የደስታ ጣዕም የሚታወቀው፤የኃዘንና የችግር ክብደት ሊቃለል የሚችለው በአንድነት ነው፤በአንድ እጅ ከመሥራት በሁለት እጅ መሥራት ለሥራው ቅልጥፍናን ይሰጣል ፤ በአንድ እግር ከመሪ መድም በሁለት እግር መራመድ በቶሎ ካሰቡት ቦታ ለመድረስ ያስችላል ። ይህ ሁሉ የአንድነት ጥቅምን የሚያስረዳ ነው ።

እንዲሁም ንቦች በመጠናቸው አንስተኞች ናቸው ። በአንድነት ሆነው የሚሠሩት ማር ግን ጣዕሙ ከሌሎች መባልዕት የጣፈጠ ነው ፤ እሳት አቃጥለን አብርተን ጨለማን በማራቅ የምንጠቀምበት ጧፍ የሚገኘው እነርሱ ከሠሩት ሰም ነው ።

የአንድነትን ጥቅም የተገነዘቡ ገበሬዎች በአንድነት አርሰው ብዙ ያመርታሉ፤ነጋዴዎችም በአንድነት በመነገድ በርከት ያለ ትርፍ ያገኛሉ ፤ ሴቶችም በበኩላቸው በአንድነት ሆነው በመፍተል የሞቀ የደመቀ ልብስ ራሳቸውና ቤተሰቦቻቸው ይለብሳሉ ።

ክቡር ዳዊት የአንድነትን ጥቅም ተመልክቶ በመዝሙር ፩፻፴፫ ቁጥር ፩ ላይ « ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሰብ ይሄልው አሀው ኅቡረ » ወንድሞች በአንድነት ቢቀመጡ እነሆ ያማረ ነው ብሏል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለሐዋርያት ወንጌልን እንዲያስተምሩ ትእዛዝዙን ያስተላለፈላቸው በአንድነት ነው እንጂ እየለያየ አንተ ሂደህ አስተምር የሚል ቃል ለአንድ ደቀ መዝሙር ለይቶ ለብቻ አልተናገረም አንድነት የሌለው ሰው ለስብከተ ወንጌል እንቅፋት መሆኑን ሲናገር «ዘኢኮነ ምስሌየ ዕድውየ ውእቱ ወዘኢይትጋበዕ ምስሌየ ውእቱ ይዘርወነ» ብሏል ትርጓሜውም ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል ከእኔ ጋርም የማይከማች ይበትናል ማለት ነው ።

ዓለሙ በጠቅላላ የአንድነትን ጥቅም በመረዳቱ በአንድነት እየተሰበሰበ ረኃብ፤ድንቁርና፤በሽታ የመሳሰሉት የሰው ልጅ ጠላቶች፤ሁሉ ከገጸ ምድር ፈጽመው የሚወገዱበትን መንገድ በመቀየስ ላይ ይገኛል ።

በመንፈሳዊም በኩል ቢሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በመካከላቸው የነበረውን አንዳንድ አለመግባባት ወደጐን ትተው በየጊዜው እየተሰበሰቡ ስለዓለም ሰላም ስለቤተ ክርስቲያን እድገት ስለ ሰው ልጅ መብትና እንዲሁም ስለ ልዩ ልዩ ችግሮች በመወያየት አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን በውሳኔ እያጸደቁ ለዓለም ነገሥታት በማቅረብ ያለባቸውን መንፈሳዊ ግዴታ ይፈጽማሉ ።

አንድ ተመራማሪ ሊቅ ስለ አንድነት ጥቅም ሲናገር « የሰው ልጆች የተፈጠሩት በአንድነት ሆነው እርስ በርስ እንዲረዳዱና የኑሮን ቀንበር አብረው እንዲሸከሙ ነው ኑሮ የጋራ ነው መኖርም ደስታውንም ችግሩንም በአንድነት ለመካፈል ነው በአንድነትም ውስጥ የግል የሆነ ነገር የለም አንዱን የሚመለከተው ሌላውንም ይመለከተዋል የጥቂቶች ኃይል የሁሉም ኃይል ነው፤የጥቂቶቹም ድካም የሁሉም ድካም ነው ከሠራተኞችና ከታታሪዎች ጋር በኖርን ቁጥር ሠራተኞችና ታታሪዎች እንሆናለን የእነርሱ ኃይል እኛንም ያነሣናልና » ብሏል ።

አንድነት ያለው ሕዝብ በሥራ ብቻ ሳይሆን በሞራልም ጠንካራ በመሆኑ ለጠላቱ ሊበገር አይችልም « ጠላቶቻችን ድል መትተን በሰላም እንድንኖር ዋስትና ሊሰጠን የቻለው የሀገራችንና የሕዝባችን አንድነት ነው » ሲል አንድ ምሁር ተናግሯል ።



ሀገራችንም ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯ ተከብሮ ፤ነፃነቷ ተጠብቆ የኖረችውና የምትኖረው በአንድነት የሚያምኑ መንፈሰ ቆራጦች የሆኑ ጀግኖች ልጆች ስለአሏት መሆኑ የሚያጠራጥር ነገር አይኖርም ።

ወደ መንፈሳዊ ክፍልም መለስ ብለን ስንመለከት ለአንድነት ተግባር ተቀዳሚ የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አንድነት የነፃነት መሠረት መሆኑን አውቃ ላላወቁት ለማሳወቅ በንቃት ታስተምራለች፤ እንዲሁም በየጊዜው ካህናትን እየሰበሰበች አንድነታቸውን አጠንክረው የወንጌልን ቃል ለሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲያሰራጩ መንፈሳዊ መልዕክትን ታስተላልፋለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ድርጅት መስከረም ፲፭ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ/ም/ የተመሠረተበትን ሃያኛ ዓመት መታሰቢያ ባከበረበት ጊዜ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት «አንድነት ኃይል ነው ብርቱው ደካማውን ሊያበረታው ልባሙም ሰነፉን ሊያነቃቃው የሚችለው አንድነት ሲኖር ነው» ካሉ በኋላ ድርጅቱ በሃያ ዓመት ውስጥ ያደረገውን የሥራ እርምጃ አመስግነዋል ።

ቅዱስነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል ለወደፊት ድርጅቱ ከዋናው ቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌል መምሪያ ጋር ተዋህዶ ቢሠራ ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚችል መሆኑን በማውሳት አባታዊ መመሪያን አስተላልፈዋል ።

ቅዱስነታቸው እንደተናገሩት አንድነት ጥርጥር የሌለበት ታላቅ ኃይል ነው ፤ በአንድነት መሥራት ዕውቀትን ያዳብራል እንጂ አይቀንስም ፤ በአንድነት መሥራት ንቁ ያደርጋል እንጂ አያሰንፍም ፤ በአንድነት መሥራት በኃይል ላይ ኃይልን ይጨምራል እንጂ ኃይልን ሊቀንስ አይችልም ።

ስለዚህ የኦርቶዶክስ እምነት እንዲጸና የወንጌል ቃል ለሁሉ እንዲዳረስ በአንድነት ለስብከተ ወንጌል እንነሣ አንድነት ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ታላቅ ኃይል ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

# የአርባ ቀን ጉዞ ለአርባ ዓመት

አርባ ቁጥር ለተለያዩ ብዙ ነገሮች የገደብ ቁጥር ነው ። በአይሁድ ሥርዓት ጾም ፤ ንስሐና ቅጣት አብዛኛውን ጊዜ በአርባ ቁጥር የተወሰኑ እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል ብዙ ሰዎች አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመዋል ፤ ንስሐም ገብተዋል ። ስለዚህም የሙሴንና የኤልያስን ጾም ማስታወስ ይበቃል (ዘጸአ- ፳፬ ፡ ፲፰ ፩ኛ ነገሥ ፲፱፥፰) አርባ ቁጥር ለብዙ ምክንያት ሁሉ ገደብ ቢሆንም በዚህ ርእስ ለመግለጥ የተፈለገው የቅጣት ገደብ ስለመሆኑ ብቻ ነው ።

በኖህ ዘመን ዓለም በነፈረ ውሃ እንደተቀጣ የተጻፈው ታሪክ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊነቱም ተረጋግጦአል ። የቅጣቱም ውሃ የዘነመው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ነበር (ዘፍ ፯፡ ፬፡ ፰ ፡ ፯)

ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰዎች ሁሉ የተቀበሉት ቅጣት ሲሆን ከዚህ በኋላ እስራኤላውያን የተቀጡባቸው አንዳንድ ታላላቅ ቅጣቶች ከአርባ በአልበለጠና ከአርባ በአላነሰ ቁጥር ተወስነው ይገኛሉ ። ለምሳሌ እስራኤላውያን በምድረ ግብጽ በባርነት ቀንበር ሥር ሆነው ለአራት መቶ ዓመታት ተጨቁነው ተገዝተዋል ። ፬፻ ዓመት በ፵ ሲቀመር ዐሥር ቀመር ወይም ፲ ጊዜ አርባ ይሆናል ። (ዘፍ ፲፭፥፲፫) እስራኤላውያን በቀድሞው ዘመን ከተቀጡባቸው ቅጣቶች ሁሉ በእነዚህ በአራት መቶ ዓመታት ውስጥ የተቀበሉአቸው መከራዎች እጅግ ይበልጣሉ። እግዚአብሐር ራሱ «የሕዝቤን መከራ ሰማሁ ጩኸታቸውን ተመለከትሁ» እስከማለት የደረሰው በእነዚህ ዘመናት ነው ። ይህም በአርባ የተቀመረው ፬፻ ዘመን የመከራ ወይም የቅጣት ጊዜ መሆኑን ያመለክታል ። ለዚህም ምክንያት የሆነው እስራኤላውያን ወንድማቸው የሴፍን እንደከብት ለ፳ ብር መሸጣቸው ነው በግልጥ አነጋገር በዮሴፍ ላይ ግፍ ስለፈጸሙ አርባ ተገረፉ ማለት ነው ።

አንድ ሰው ወንጀለኛ ሆኖ ሲገኝ አርባ ጊዜ በጅራፍ እንዲገረፍ የሙሴ ሕግ ያዝዛል ። ከአርባ በላይ መቅጣት ግን ክልክል እንደሆነ በዚሁ ሕግ ተመልክቶአል ። የሕጉ ቃል በሙሉ እንደሚከተለው ነው ። «በደለኛው መገረፍ ቢገባው እንዲገረፍ ፈራጁ በፊቱ በምድር ላይ ያጋድመው የግርፋቱም ቁጥር እንደ ኃጢአቱ መጠን ይሁን። ግርፋቱም አርባ ይሁን ። ከዚህ በላይ ጨምሮ ብዙ ግርፋት ቢገርፈው ወንድምህ በፊትህ ነውረኛ ይሆናልና ከዚህ በላይ አይጨመርበት (ዘዳግም ፳፭ ፤ ፪—፫ በዚህ ሕግ መሠረት ቅዱስ ጳውሎስ ፭ ጊዜ ተገርፎአል ፪ኛ ቆሮ ፲፩ ፡ ፳፬ ።

እስራኤላውያን ለ፬፻ ዓመታት በግብጽ በመከራ ከኖሩ በኋላ እግዚአብሐር በሙሴ መሪነት ነፃ አወጣቸው። ግን ነፃነታቸውን ወደ ባርነት ለመለወጥ ነፃ ያወጣቸው እግዚአብሐርን በፍጹም ልባቸው አልተከተሉም በሙሴ በኩል የተላለፈላቸውን ቃሉን አላመኑም ።

ለምሳሌ ወደ ሀገራቸው ወደ ከነዓን እንደሚገቡ የተነገራቸውን ተስፋ ተጠራጠሩ ። በውሃና በምግብ ምክንያት ብዙ ጊዜ እግዚአብሐርን ተፈታተኑ ። መሪዎቻቸው ሙሴንና አሮንን ለመግደል አያሌ ጊዜ ሙከራ አደረጉ ፤ ከዚህም ሁሉ በላይ ከግብጽ ያወጣቸው እግዚአብሐርን በማምለክ ፋንታ የወርቅ ጥጃ ሠርተው አመለኩ። በዚህም ሁሉ ጥፋታቸው እግዚአብሐር ሊቀጣቸው ፈለገ ። ቅጣታቸውንም በአርባ ቁጥር ወሰነ ። በሲና በረሃ እስከ እስራኤል ሀገር በዚያ ዘመን በእግር የአርባ ቀን ጉዞ ሲሆን ለአርባ ዓመታት በጉዞ እንዲኖሩ አድርጎ ቀጣቸው ።

የቅጣቱ ውሳኔ እንዲህ ይላል «በግብጽ ምድርና በበረሃ ያደረጉሁትን ተአምራቴንና ክብሬን ያዩ እነዚህ ሰዎች ሁሉ አሥር ጊዜ ስለተፈታተኑኝ ቃሌንም ስላልሰሙ በእውነት ለአባቶቻቸው የማልሁላቸውን ምድር አያዩም .... ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያ በላይ የሆነ ሁሉ ወደ ተስፋ ሀገር አይገባም» (ዘኊል ፲፬ ፡ ፳፪—፴) በመጨረሻም «... ስለ አንድ ቀን አንድ ዓመት ኃጢአታችሁን አርባ ዓመት ትሸከማላችሁ ቁጣዬንም ታውቃላችሁ » (ዘኊል ፲፫፡፴፬) የሚለው ፍርድ በቁጥር ተነገራቸው ።

በዚህ ዓይነት ቅጣት የአርባው ቀን ጉዞ ወደ አርባ ዓመት ተራዝሞ ሲሄዱ የዋሉትን ተመልሰው ሲሄዱ በማደር በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋወረ መንገድ ሲንከራተቱ ኖረዋል ።

እስራኤላውያን ያን ጊዜ አርባ ዓመት የተጓዙት መንገድ ዛሬ ከካይሮ እስከ ቴላቢብ በተሠራው መንገድ በአውቶቡስ የስምንት ሰዓት ጉዞ ነው ። ርቀቱም በኪሎ ሜትር ከስዊዝ ካናል እስከ እስራኤል ሀገር ፪፻፺ ያህል ነው። ዛሬም ይህን ርቀት በእግር ለመጓዝ ከአሥር ቀን ያልበለጠ እንደማይወስድ ይገመታል ።

ነገር ግን በዚያ ዘመን የአርባ ቀን ጉዞ እንደሚሆን መገመቱ እስራኤላውያን ሕጻንና ሽማግሌ እያስዘገሙ ትብትብ ጓዝ እየተሸከሙ በሽተኞችን እያስታመሙ ይጓዙ ስለነበር ነው ። ከዚህም ሌላ ብዛታቸው እጅግ ብዙ ነበር ። ከሕፃናትና ከሴቶች ሌላ ስድስት መቶ ሦስት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ነበሩ ። ይህም ሌዋውያንን አይጨምርም ከዚህ ሁሉ ሕዝብና ጓዝ ጋር አርባ ቀናት ብቻ ይወስድ የነበ

ተከታዩ ወደ፯ኛው ገጽ ዞሯል



# ተራዳኢው መልአከ ቅዱስ ሚካኤል

የእርዳታ መልክ ዓይነቱ ብዙ ነው። አንደኛው የገንዘብ እርዳታ ሲያደርግ ሌላው ደግሞ የቁሳቁስ ፤ ሌላው የሞራል ፤ የጉልበት የመሳሰሉትን ችግር ለደረሰባቸው ሁሉ ሲፈጸም ይታያል። ባጭሩ የእርዳታ መልኩ ይህን ሲመስል በአንፃሩ ደግሞ ከመከራ ከፈተና ለአደጋ ከጠላትም ተዋግቶ ነፃ የማውጣትም እርዳታ አለ ።

ይህ ከሆነ ተራዳኢው ቅዱስ ሚካኤል በየትኛው መንገድ ማንን ረድቷል ? የረዳቸውስ እነማን ናቸው ? የረዳበትስ ቦታ የት ነው ? ዘመኑስ መቼ ነበር ? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል ። መልሱም ለሦስት ዓመታት ያህል ደጋግሞ አገሩን ድርቅ ስላጠቃው ያዕቆብ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ምስር ተሰደደ በዚያም የሱ ልጆች እየተባዙ ብዙ ሕዝብ ለመሆን ቻሉ ። ታሪክ እንደሚነግረን በየጊዜው የሚነግሡት ፈርዖኖች በነሱ ላይ ግፍና መከራ ያጸኑባቸው ጀመር፤ ከባርነት ቀንበር የሚያወጣቸውና ረዳትም የሚሆናቸው ስለአስፈለጋቸው ። እንባቸውንና ጸሎታቸውን ወደ እግዚአብሔር አቀረቡ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰማ ።

ለአራት መቶ ሰላሳ ዓመት ያህል የእስራኤል ሕዝብ በስቃይና በመከራ አገዛዝ ከቆዩ በኋላ በ፫ሺ፬፻፺፰ ዓመተ ዓለም ሙሴ የእስራኤልን ነገድ ከምስር በእግዚአብሔር ትእዛዝ አወጣቸው ። በተጨማሪም እግዚአብሔር የሚጠብቃቸውና የሚረዳቸው የሚመራቸውም መልአክ ሰጥቶአቸው ነበር ። ስለዚህም ታላቁ መጽሐፍ እንደሚከተለው ያብራራዋል ።

ከእስራኤልም ሠራዊት ፊት ይሄድ የነበረው የእግዚአብሔር መልአክ ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ሄደ የደመናውም ዓምድ ከፊታቸው ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ቆመ በግብፃውያን ሰፈርና በእስራኤል ሰፈር መካከልም ገባ በዚያም ደመናና ጨለማ ነበር በዚህ በኩል



እስራኤል ፡ ኤርትራን ፡ ሲሻገሩ ፡ ግብጻውያን ፡ እንደሰጠሙ ፡ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፳፱ ።

ግን ሌሊቱን አበራ ሌሊቱንም ሁሉ እርስ በርሳቸው አልተቃረቡም» ይላል ። ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፲፬ ቁጥር ፲፱—፳ ።

አሁን የተጠቀሰው ጥቅስ የእግዚአብሔር መልአክ ከማለት በቀር የእስራኤልን ሕዝብ ከእግዚአብሔር ተልኮ ከችግራቸው የረዳቸውና ያዳናቸው የመራቸውም የትኛው መልአክ እንደሆነ ስሙን አይጠቅስም ። ቅዱስ ሚካኤል መሆኑንም አይናገርም የሚል ጥያቄ ቢቀርብ መልሱ እንደሚከተለው ይሆናል በዘመነ ሐዲስ በአምስተኛው መቶ ዓመት የተነሣው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ከላይ የተጠቀሰውን የብሉይ ኪዳን ቃል ሳይ



www.ethiopianorthodox.org

ለቅ በዘመን አስተምህሮ ድጓ የሚከተለውን ተናግሮአል ።

«መርሆሙ መዓልተ በደመና ወኩሎ ሌሊተ በብርሃነ እሳት ወአውጽአሙ ለሕዝቡ በትፍሥሕት ፈነወ መልአኮ ወእድኅኖሙ እንዘ ሚካኤል የሐውር ቅድመ ትእይንቶሙ ለእስራኤል »

«ትርጉሙ ቀን በደመና ፤ ሌሊቱን ሁሉ በብርሃነ እሳት መራቸው ። ሕዝቡንም በደስታ አወጣቸው ። መልአኩን ልኮ አዳናቸው ። እሱም ቅዱስ ሚካኤል ሲሆን በእስራኤል ፊት ለፊት ይሄድ ነበር» ማለት ነው ። ይህ ከሆነ የእግዚአብሔር መልአክ የተባለውን ሊቁ ያሬድ ቅዱስ ሚካኤል መሆኑን መስክሮለታል ። ይህም በመሆኑ ከእግዚአብሔር የታዘዘው ቅዱስ ሚካኤል ሞልቶ የነበረውን የቀይ ባህርን ውኃ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስን በእግዚአብሔር ኃይል እሥነስቶ አስወግዶው ባህሩን እንዲደርቅ አደረገው ውኃውም በሙሴ እንዲከፈል ሆነ የእስራኤል ልጆችም በባህሩ መካከል በየብሱ ገቡ ውኃውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው »

የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር ለምሕረትና ለረዳትነት በላከው በቅዱስ ሚካኤል እየተጠበቁ ቀይ ባህርን በሰላም ተሻገሩ «እግዚአብሔርም ሙሴን በባህሩ ላይ በትሩን እንዲዘረጋ እዘዘው ውኃውም በግብፃውያን በሰረገሎቻቸውም በፈረሰኞቻቸውም ላይ ይመለስ አለው ። እግዚከብሔርም ግብፃውያንን በባህሩ መካከል ጣላቸው ውኃውም ተመልሶ ኋላቸው ወደ ባህር የገቡትን ሰረገሎችን ፈረሰኞችንም የፈርዖንንም ሠራዊት ሁሉ ከደነ ከእነሱ አንድስ እንኳ አልቀረም» ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፲፬ ከቁጥር ፳፩ እስከ ፳፰

ይህም የሚያሳየን የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሆነው ቅዱስ ሚካኤል የሚላከው ለምሕረት ፤ ለቸርነት ፤ ለበጎ ነገር ፤ ደጋግ ሰዎችን ለመርዳት ብቻ ሳይሆን ለመቅሠፍት ለመዓት ፤ ለቁጣ በክፉ ሰዎችም ላይ የእግዚአብሔርን ኃይል ለማሳየት የሚላክ መሆኑንም ነው ። ይህም የሚታወቀው በባርነት ቀንበር ተይዘው ፤ በግፍና በመከራ ለብዙ ዘመን ሲሰቃዩ የኖሩት የእግዚአብሔር ልጆች የእግዚአብሔር መልክተኛ ከሆነው ከቅዱስ ሚካኤል ዘንድ ታላቅ እርዳታንና መልካም አጠባበቅን አግኝተው በሰላምና በሕይወት ቀይ ባህርን ሲሻገሩ ፤ በእስራኤል ልጆች ላይ ግፍና መከራን እየፈጸሙ በምቾት የኖሩት ግብጻውያን ግን በቅዱስ ሚካኤል አማካይነት እንደ ሥራቸው ዋጋቸው ተከፍሎአቸዋል «ሁሉ እንደ ሥራው ይከፈለዋል» ተብሏልና ።

ይህም በመሆኑ መጋቤ ብሉይ እየተባለ የሚጠራው ቅዱስ ሚካኤል የእስራኤል መልአክ ፤ የሕዝበ እስራኤል እረዳት ፤ የያዕቆብ ልጆች ጠባቂ ፤ መሪና ፈጥኖ ደራሽ መሆኑን ባደረገው ተአምር ለማወቅ ይቻላል ። ስለዚህም መዝሙረኛው ዳዊት መልአኩ ስለሚያደርገው እርዳታና ደኅንነት «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል» በማለት ዘምሮአል መዝሙር ፴፫ ቁ/ ፯ ። ዳዊት ይህንን የዘመረለት የእግዚአብሔር መልአክ የእስራኤል ሕዝቦች ከጠላቶቻቸው ለማምለጥ በሚኀዙበት ወቅት ፤ በየሥፍራው እየከተሙ በሚሠፍሩበት ሥፍራ ሁሉ ከጠላቶቻቸው ያዳናቸውና የረዳቸው ቅዱስ ሚካኤል መሆኑን የኢትዮጵያ ሊቃውንት በአንድምታ ትርጓሜ ያትቱታል ።

ከላይ በጠቀስነው ዘመን ከአርባ ዓመት በኋላ ደግሞ ኢያሱንና ወደ ምድረ እርስት የሚመራቸውን ሕዝቦች ቅዱስ ሚካኤል እንደረዳቸው እንመለከታለን «ኢያሱ ኢያሪኮ አጠገብ ደርሶ ሳለ የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው ከፊቱ ቆሞ አየ ኢያሱም ከኛ ነህን ? ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ሲል ጠየቀው እርሱም አይደለሁም እኔ ከእግዚአብሔር የሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ አለ ። እያሱም በግንባሩ ወድቆ ሰገደለት » መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ ፭ ቁጥር ፲፫ ።

ይህንንም አባ ዮሐንስ ዘቡርልስ እና አባ ሚካኤል ዘሀገረ አትሬብ የተባሉ መንፈሳውያን ደራሲዎች በጻፉት በየዓመቱ ኅዳር ፲፪ ቀን የሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር እንደሚከተለው ወስዶታል ኢያሱ ኢያሪኮ አጠገብ ሲደርስ የመላእክት አለቃ የሆነው ቅዱስ ሚካኤልን ሠይፉን መዞ በሰው አምሳል አየው ከኛ ነህን ወይስ ከጠላቶቻችን ብሎ ቢጠይቀው የሚዋጉህን አማሌቃውያን እጅህ እጥልልሀለሁ በኢያሪኮም ላይ እሾምሐለሁ ሲል ነገረው ጠላቶቹንም አጠፋለት ታላቅ እርዳታም አደረገለት ስለዚህ በየዓመቱ በዓሉን እንድናከብረውና እንድናስበው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አዘውናል » ሲሉ ጽፈዋል ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ይህን መሠረት በማድረግ ኅዳር ፲፪ ቀን በየዓመቱ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል ታቦቱ በተተከለበት ስሙ በሚጠራበት ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በጸሎት በማኅሌት፤ በቅዳሴ ያደረገውን እርዳታና በየጊዜው ከእግዚአብሔር ዘንድ እየተላከ ለሰዎች የሰጠውን መልካም አገልግሎት እያስተማረች ታስበዋለች ክርስቲያኖችም በቦታው እየተገኙ ጸሎት ከማድረሳቸውም ሌላ ስዕለት እያቀረቡ ያደረገላቸውን እርዳታ በምስጋና ይገልጣሉ ።

በተጨማሪም በ፶፭ ዓመተ ዓለም ክሌዎፓትራ የተባለችው ንግሥት ዙሐል ለተባለው ጣዖት ታላቅ መቅደስ አሰርታለት ነበር ። ይህም ለብዙ ዘመን ሲያያዝ የመጣ በመሆኑ ሕዝቡ ይወደውና ያመልከው ነበር ።

በየዓመቱ ኅዳር ፲፪ ቀን የዙሐል በዓል ስለሚከበር ሕዝቡ ሁሉ ተሰብስቦ በዓሉን ከማክበሩም ሌላ ብዙ ስለት ያቀርባል ፍሪዳ እያረደ እየበላ እየዘፈነ እየተጫወተ ሲያከብረው ይውላል ይህም ድርጊት እስከ ክርስትና ዘመን ቆይቶ ነበር ። ቅዱስ ማርቆስም ወንጌልን እየሰበከ ሌሎቹን ጣዖታት ሲደመስስ ዙሐልን ግን ማጥፋት አልቻለም ዙሐልም በሕዝቡ ዘንድ እየተመለከ እስከ ፫፻፳ ዓመተ ምህረት ድረስ ቆየ እለ እስክንድሮስ የተባለው ጳጳስ ዘዴኛና ብልህ ስለነበር ሕዝቡን አስተምሮና አሳምኖ ኅዳር ፲፪ ቀን በዙሐል ፋንታ የቅዱስ ሚካኤል በዓል እንዲከበር አደረገ ።

ይህም ቅዱስ ተግባር በሕዝቡ ዘንድ ስለተጠና ዙሐል እየተረሳ ፤ ቅዱስ ሚካኤል እየተወደደ ሄደና የቅዱስ ሚካኤል በዓል ኅዳር ፲፪ ቀን በየዓመቱ መከበር እየተለመደ ሄደ ይህንንም ሰኔ ፲፪ ቀን በሚነበበው ድርሳነ ሚካኤልና መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት በተባለው መጽሐፍ ፩፻፳ ገጽ መመልከት ይቻላል ።

አባ ሰላማ የቤተ ክርስቲያንን ሥነ ሥርዓት ወደ ሀገራችን ይዞ ሲመጣ ኅዳር ፲፪ ቀን በየዓመቱ የሚከበረውን የቅዱስ ሚካኤልን በዓልና ሥነ ሥርዓት ይዞ እንደመጣ ይነገራል ። በየወሩ የሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል በዓል ግን የተወሰነው በ፲፬ተኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ይታወቃል ።

እንግዲህ ክርስቲያኖች የሆንን ሁሉ በየዓመቱ ኅዳር ፲፪ ቀን የቅዱስ ሚካኤል በዓል የሚከበርበት ዕለት ስለሆነ ታቦቱ በተተከለበት መቅደሱ በታነፀበት እየተገኘን መሳለም ይገባናል የተቸገሩትን መርዳት የተማጸኑትንም ማማለድ ለሰዎችም አገልግሎት [illegible]ጠት ተግባሩ ስለሆነ ቅዱስ ሚካኤል እኛን እንዲረዳን እኛ ደግሞ በተቻለን መጠን ድሆችን እንርዳ እርስ በርሳችንም እንዋደድ ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## የአርባ ቀን ጉዞ ...

ከ፬ኛው ገጽ የዞረ

ረው መንገድ ለአርባ ዓመት መሆኑ የሕዝቡን የኃጢአት ብዛትና የእግዚአብሔርን ፈራጅነት ያመለክታል ። እግዚአብሔር ፈታሒ በጽድቅ (በእውነት ፈራጅ) ስለሆነ በኃጢአተኛው እንደ ፈራጅነቱ ይፈርድበታል ለጻድቁም እንደ መሐሪነቱ ይፈርድለታል።

እግዚአብሔር በመዓቱ አንዱን ቀን አንድ ዓመት እንደሚያደርግ በምሕረቱ ደግሞ አንዱን ዓመት እንደ አንድ ቀን በመቁጠር አርባውን ዓመት እንደ አርባ ቀን ያደርጋል ። ይህንም ከትንቢተ ሕዝቅኤል ፬ ፡ ፮ መረዳት ይቻላል ። ቃሉም ይህ ነው «---- በቀኝ ጐድንህ ትተኛለህ የይሁዳንም ቤት ኃጢአት ትሸከማለህ አንድን ዓመት አንድ ቀን አድርጌ አርባ ቀን ሰጥቼሃለሁ»

ለማጠቃለል ያህል እግዚአብሔር ካልፈቀደ ሰው በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲከናወንለት የሚያቅደው ነገር ሁሉ ረዥምም ጊዜ ሊወስድ ይችላል ። እግዚአብሔር ሲፈቅድ ደግሞ ብዙ ጊዜ ይወስዳል ተብሎ የሚገመተው ነገር በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍጻሜን ያገኛል ። ሰው ለአጭርና ለረዥም ጊዜ የሚያወጣው ዕቅድ ሁሉ በእግዚአብሔር ሥልጣን የተወሰነ ነውና። የሰውና የእግዚአብሔር ሀሳብ የተለያየ ነው ለምሳሌ ወደ ተስፋዋ ሀገር ይገባሉ የተባሉት የእስራኤል ሽማግሎች በሲና በረሃ እንደ ቅጠል ረግፈው ሲቀሩ በጠላት ተማርከው ይቀራሉ በረኃብና ጥም ተጐድተው ያልቃሉ የተባሉት ከሃያ ዓመት በታች የነበሩት ወጣቶች የተስፋዋን ሀገር ወረሱ የአርባውም ቀን ጉዞ ወደ አርባ ዓመት የተራዘመው ይህ አይነቱ ፍትሐ እግዚአብሔር ይፈጸም ዘንድ ነው ። እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች የመከራን ዘመን ሲያረዝም ለወዳጆቹ ግን ቀናቱን ያሳጥራልና ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

---

## ደብዳቤዎች

ከ፭ኛው ገጽ የዞረ

ጣሁአይመስላችሁ ሰይፍን እንጂ ሲል የተናገረው ቃል ግልጽ ነው ሥውርም አይደለም አንድ ሰው ፲ ልጆች ይወልዳል ከአሥሩ አምስቱ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምኑ አምስቱ ደግሞ ላያምኑ ይችላሉ በዚህ ምክንያት አማኞችና ያላመኑት በሃይማኖት ስለሚጣሉና ስለሚለያዩ ይህን ለመግለጽ ነው ። እንጂ ጌታስ የመጣው ለፍቅርና ለሰላም ነው ።

እርግጥ አሁንም እንደ ሆነ ያመነ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ሲወርስ ያላመነ ሰው ግን የገሃነም ሰይፍ ይመዘገበታል ማለት ነው ። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለፍቅር እንጅ ለጠብ እንዳይደለ በተጠቀሱት ጥቅሶች እንደም ትረዳ እምነታችን ፍጹም ነው ።

፫ኛ/ ጥያቄ በጽሑፉ እንደምንረዳው ያች ሲጾናዊት ሴት በኋላ በኋላው እየተከተለች ብትጮህበት ከእሥራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም ሲል እንደ መለሰላት እንገነዘባለን ።

ሕዝበ እግዚአብሔር ተብለው ይጠሩ ለነበሩ እሥራኤላውያን እንዲህ የሚል ትንቢት ተነግሮላቸው ነበር ። « እርሱ ራሱ ሰው ሁኖ ወደዚህ ዓለም ይገባል ( ይመጣል) እኔ ሰው ሁኖ ያየሁት ከባሕርይአባቱም ወደዚህ ዓለም የተላከ ሰው ሁኖም ወደዚህ ዓለም የመጣ እርሱ አብሮአቸው ይታይና ይገለጥላቸው ዘንድ ፲፪ ሐዋርያትን ይመርጣል» ተብሎ ትንቢት የተነገረላቸው ለእሥራኤላውያን እንጂ ለአሕዛብ አልነበረም ።

ስለዚህ ያች ሴትም በቡችላ ልትመስል የቻለችው በመጀመሪያ መሠረተ እምነት ስላልነበራት ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# ክርስቲያኖች የትንሣኤን በዓል ለምን በአንድ ቀን አያከብሩም ?

ከሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው

ይህ ክርስቲያኖችንና የሌሎች እምነት ተከታዮችንም የሚያስገርምና መልስ ያልተገኘለት ከባድ ጥያቄ ነው ። በቀላሉ የሚወገድ ችግር ባለመሆኑ ለእያሌ ዘመናት ሲያከራክር ቆይቷል ። ልዩነቱ የተፈጠረው በቤተ ክርስቲያን መለያየት ነው ባይባልም ችግሩን ከታሪክ ጋር ሲመረምሩት ከዚሁ አካባቢ የራቀ አይደለም ሌላው ቀርቶ የሚያሳዝነው ክጥንታውያት አብያተ ክርስቲያናት ኦርቶዶክሳውያንና ካቶሊኮች እንኳን አንድነት የትንሣኤን በዓል አያከብሩም ። የሚከተለውን በጥሞና ያስተውሏል ።

ለዚህም ችግር መፈጠር ዋና ምክንያት የሆነው የተለያዩት አብያተ ክርስቲያናት በየበኩላቸው የዕለቱን ችግር እናስተካክላለን ሲሉ የተለያየ ውጤት በማግኘታቸው ነው ።

የትንሣኤ በዓል አከባበር ጥንተ ሥርዓቱ እንደዚህ ነበር ።

የትንሣኤ በዓል ታላቁና ጥንታዊው እንደመሆኑ ሁሉ መከበር ከተጀመረበት ዘመን አንሥቶ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በዓሉ የሚከበርበት ዕለት ጉዳይ ጥያቄን ስላስከተለ በአንዳንድ ሲኖዶሶች በውይይት ላይ ቆየ።

ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት ፵፭ ዓመተ ዓለም ፣ ተስተካክሎ የነበረውና በስሙ የዩሊየስ ካሌንደር እየተባለ የሚጠራው የቀን መቁጠሪያ በ፫፻፳፭ ዓ-ም በጉባኤ ኒቂያ ሲመረመር ፫ ቀናት ጉድለው ተገኙ ። ይህም ሲታሰብ በየ፩፻፳፰ ዓመት አንድ ቀን ወደ ኋላ ይቀራል ማለት ነው ። በዚህም ምክንያት የኒቂያ ጉባኤ በ፫፻፳፭ ዓ-ም ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ወደኋላ ቀርቶ የተገኘውን የዩሊየስ ካሌንደር አስተካክሎ «የትንሣኤ በዓል በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ፣ በኒቂያ ዘመነ ጽጌ (የጥቢ ወራት) በመጋቢት ወር ጨረቃ ሙሉ ስትሆን ፣ ቀንና ሌሊቱ እኩል ከሚሆንበት ዕለት ቀጥሎ ባለው እሁድ እንዲከበር ፣ ግን የአይሁድ ፋሲካ እንዳጋጣሚ በዚህ ዕለት ቢውል ከዚያ ቀጥሎ ባለው እሁድ ትንሣኤ ይከበር» ስላሉ ይህ ሥርዓት ለእያሌ ዘመናት ሲሠራበት ኖረ ።

እንግዲህ የመጀመሪያው የትንሣኤ በዓል የዋለበት እሁድ ከአይሁድ ፋሲካ ፲፬ ቀን ኒሳን በሚባለው ወር ሦስተኛው ቀን እንደነበረ አራቱም ወንጌላውያን በጻፉት እንረዳለን ።

በርባን የተፈታበት ክርስቶስ የተሰቀለበት ዕለተ ዓርብ የአይሁድ ፋሲካ እንደነበረ ስለተጻፈ ነው ። በዚያም የትንሣኤ ዕለት እንዳጋጣሚ ቀንና ሌሊቱ እኩል ከነበረበት ዕለት በኋላ የዋለው የሙሉ ጨረቃ እሁድ እንደ ነበር በቀመሩ ታውቋል ።

የትንሣኤ በዓል የአከባበር ስነ ሥርዓት ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ ሲሠራበት የቆየ ስለነበረ በኒቂያ ጉባኤ ጸንቷል ። የተስተካከለው ከዩሊየስ የቀን አቆጣጠር የጐደለው የሦስት ቀን ልዩነት ብቻ ነው ።

ማስረጃ የሐዋርያት ቀኖና (አብጥሊስ) አንቀጽ ሰባት «የትንሣኤን በዓል መዓልቱና ሌሊቱ እኩል ከሚሆንበት በመጋቢት ወር ከአይሁድ ፋሲካ በፊት የሚያከብር ጳጳስ፣ ቄስ ወይም ዲያቆን ከሹመቱ ይሻር» ይላል። እንዲሁም በጉባኤ አንጾኪያ ፫፻፴፩ ዓ-ም በተደነገጉት ቀኖናዎች አንቀጽ ፩ «በቡሩኩና በመፍቀሬ እግዚአብሔር ንጉሥ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ሰብሳቢነት የተወሰነውን የቅዱሱንና ታላቁን የኒቂያን ጉባኤ ስለ ደኅንነታችን የትንሣኤ በዓል አከባበር በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ያሳለፈውን ቀኖና በድፍረት ለመሻር የሚሞክሩ ምዕመናን ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ይለዩ።

በተለይም ጳጳስ ፣ ቄስ ወይም ዲያቆን በድፍረት ይህን ቅዱስ ሲኖዶስ የወሰነውን ሕግ ሽሮ የትንሣኤን በዓል ከአይሁድ ፋሲካ ጋር ቢያከብርና ለምዕመናን የብጥብጥ ምክንያት ቢሆን ከክህነቱ ይሻር ። ከቤተ ክርስቲያንም ፈጽሞ ይወገድ» ይላል ። ቤተክርስቲያን ሳትከፋፈል ሁሉም በተሰበሰቡበት የተወሰኑትን ቀኖናዎች በማክበር ክርስቲያኖች በሙሉ የትንሣኤን በዓል አንድነት እያከበሩ እስከ ፩ሺ፭፻፹፪ ዓ-ም ቆዩ ። በዚህ ዓመተ ምህረት ግን በፓፓ ጎርጎርዮስ ፲፫ኛ ጊዜ ካላንደር ሲመረመር ከኒቂያ ጉባኤ ፫፻፳፭—፩ሺ፭፻፹፪ ዓ-ም ፲ ቀን ጐድሎ ተገኘ ። ይህም በያንዳንዱ ፩፻፳፰ ዓመት አንድ ዓመት አንድ ቀን ጐድሏል ማለትነው ።

በዚህም ምክንያት ፲ ቀን ጨምረው አስተካክሉና እንደ ጎርጎርዮስ (እንደ አውሮፓ) የቀን አቆጣጠር እየተባለ የትንሣኤ በዓል በዚህ መሠረት ሲከበር የጥንቱን የተወሰነውን አንለቅም ካሉት ጋር ልዩነት ተፈጠረ ።

በውነቱ በዚህም ጊዜ ከስህተት ለመዳን አልተቻለም የተሻሻለ ነገር ቢኖር በየ፩፻፳፰ ዓመት አንድ ቀን በመተረፍ ፈንታ በየ፬ ሺህ ዓመት አንድ ቀን እንዲተርፍ ሆኖ ተስተካክሏል መባሉ ብቻ ነው ። በመጨረሻም እ/ኤ/አ/ በ፲፱፻፳፫ ዓ-ም የቪይዛንታይን ኦርቶዶክሳውያን ጉባኤ በቁስጥንጥንያ ተሰብስቦ የዩልዮስንና የጎርጎርዮስን ካሌንደር (የቀን አቆጣጠር) ከመረመረ

ተከታዩ ወደ፲፩ኛው ገጽ ዞሯል



# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ይዞታ

ከአዲስ ተረፈ ፣

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ዘመናት የትምህርት ማዕከል ሁና ኅብረተ ሰቡን ስታገለግል ኑራለች አሁንም እያገለገለች ነው ።

ከታሪክ እንደምንረዳው በሀገራችን ሥነ ጽሑፍ የተጀመረው የኦሪት እምነት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ከክርስቶስ ልደት በፊት ቀደም ብሎ ነው ። ለዚህም በአክሱም ሐውልቶች ላይ በሳባውያን ፣ በግሪክኛና በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉት ጽሑፎች የዓይን ምስክሮች ናቸው ። የአክሱም መንግሥት የአንድ ቋንቋ ባለቤት ብቻ ሳይሆን ከላይ በተጠቀሱት ዓለም አቀፍና ብሔር አቀፍ ቋንቋዎች ሥነ ጽሑፍን ለማዳበር ይጠቀም እንደነበር መረዳት ይቻላል ።

በግብረ ሐዋርያት ም- ፰ ቁ-፳፮ የንግሥት ሕንደኬ መልእክተኛ ለጸሎት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ በነበረበት ጊዜ በሠረገላ እየተጓዘ መጽሐፈ ኢሳይያስን በእብራይስጥ ቋንቋ ሲያነብ መታየቱ ተጽፏል ። ይህም ሁኔታ በአክሱም ቤተ መንግሥት አካባቢ ትምህርት ተስፋፍቶ እንደነበር የሚያስረዳ ሌላ ምስክር ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በአራተኛው መቶ ዓመት በይፋ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ትምህርትን በቁጥጥሯ ሥር አድርጋ ስትመራ ኑራለች ። በተለይም የመጀመሪያ ጳጳስ ሁኖ የተሾመው



ሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሣን ካሣ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ይዞታ ተጠይቀው ሲያብራሩ ፣

ፍሬምናጦስ ቀደም ብሎ የቆየውን ፊደል እንዲሻሻል አድርጓል እያሌ መጻሕፍት ከዕርእ ፣ ከእብራይስጥና ከቅብጥ ቋንቋዎች ወደ ግዕዝ እንዲተረጐሙ አድርጓል አብያተ ክርስቲያናት በብዛት ተተክለዋል ። በአብያተ ክርስቲያናቱም ጐን ት/ቤቶች አብረው ተስፋፍተዋል ፍሬምናጦስ ለትምህርት የነበረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ስለነበር ቤተ ክርስቲያን «ከሣቴ ብርሃን» የብርሃን ገላጭ ብላ ሠይማዋለች።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያኗ የትምህርትን ጥቅም በሚገባ ስለተረዳች ሕንፃ ሥሩልኝ በጀት ደልድሉልኝ ሳትል በደጃ ሰላም ዙሪያና በዛፍ ሥር ወንበር ዘርግታ የመጣውን ሁሉ በነፃ ስታስተምር ኖራለች ። ይህም ሊሆን የቻለው በፀጋ ያገኛችሁትን በፀጋ ስጡ የሚለውን ወንጌላዊ መርሆ በመከተል ነው ። ትምህርት ብል የማይበላው ሌባ የማይሰርቀው ሀብት ነው ። ቤተ ክርስቲያን ይህን በመረዳት ለትምህርት ቅድሚያ ትሰጣለች። ከመጠምጠም መማር ይቅደም የሚለው አነጋገር ለትምህርት የተሰጠውን ከፍተኛ ደረጃ ይገልጻል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርት በዋጋ ሊተመን የማይችል እጅግ ከፍተኛ ንብረት መሆኑን ተገንዝበው በደመወዝ ተቀጥረው ከማስተማር ይልቅ በትሩፋት ማስተማሩን መርጠው ለቤተ ክርስቲያኗ ተወዳዳሪ የሌለው አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ ኑረዋል ተማሪው በሚማርበት ጊዜ የሥርክ ኀብስት ችግር እንዳይደርስበት ኀብረተ ሰቡን በማስተባበር ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ለምኖ እንዲበላ ከምዕመናኑ ጋር ሕጋዊ ስምምነት በመደረጉ ጊዜው በሚፈቅደው ሁኔታ የትምህርቱ ዓላማ ግቡን እንዲመታ ተደርጓል ።

በዚህ ሁኔታ መምህራኑ በትሩፋት ሲያስተምሩ ተማሪው ደግሞ የነፃ ትምህርት በማግኘት ፴ እና ፵ ዓመት በኅብረተ ሰቡ ትከሻ ሲማር ይኖራል። ይህም በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው የትምህርት አመራር ዘይቤ ነው ። በዚህ ሁኔታ በመማር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ከ፪፻ ሺህ በላይ የሆኑ አገልጋይ ካህናት ሊኖራት ችሏል ይህ ሁሉ ካህን እንደ አሁኑ ገንዘብ እየተከፈለው ይማር



www.ethiopianorthodox.org

ቢባል ኖሮ ምን ያህል ገንዘብ ሊወጣ እንደሚችል የአንባብያን ሕሊና ሊገምተው ይችላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በትምህርት በኩል ያላትን ከፍተኛ ባለውለታነት በጉልህ የሚገልጸው ኢትዮጵያ ሀገራችን የግዷ የሆነ የፊደል ባለቤት እንድትሆን ማድረጓ ነው ። በአፍሪካ አህጉር ከሚገኙት ሃምሳ ሦስት ነፃ ሀገሮች ፊደል ያላትና በራሷ ቋንቋ የምትሠራ ኢትዮጵያ ብቻ ናት ። ይህም ከቤተ ክርስቲያኗ የተገኘ በረከት ለመሆኑ ለማንም የተሠወረ አይደለም ።

በዚያ በጨለማው ዘመን የኅትመት መኪና ከመፈልሰፉ በፊት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ብራና ፋቀው ቀለም በጥብጠው ብርዕ ቀርጸው ዓይናቸው እስኪፈዝ ጉልበታቸው እስኪደነዝዝ ቆጥ ብለው ጉልቆ መሣፍርት የሌላቸው መጻሕፍትን ጽፈው አልፈዋል ።

እነዚህ መጻሕፍት እንዳንዶቹ በስጦታ መልክ ፤ አንዳንዶቹ በግዥ ፤ አንዳንዶቹም በዘረፋ መልክ ከሀገር ውጭ ስለወጡ በሥነ ጽሑፍ ዓለም ኢትዮጵያ ሀገራችን በወርቅ ቀለም እንድትጻፍ አድርገዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በዘመናት መካከል ማይምነትን ስትዋጋ ኑራለች ገዳማትና አድባራት ከፍተኛ የትምህርት ማዕከሎች ብቻ አልነበሩም በአሁን አነጋገር የመሠረተ ትምህርት ጣቢያ በመሆን ትምህርት ፈላጊውን ሁሉ እንደየፍላጐቱ ሲያስተናግዱ ኑረዋል ። በአሁኑም ወቅት ቤተ ክርስቲያኗ የብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ኮሚቴ ቋሚ አባል በመሆን በአገር አቀፍ የተዘረጋው ፀረ መሃይምነት ዘመቻ ተሰልፋ ድንቁርናን በማጥፋት ላይ ትገኛለች ።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ይዞታ በምን ላይ እንዳለ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ ኃላፊ ከሆኑት ከሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሳን ካሣና ከዚሁ መምሪያ ም/ኃላፊ ከቀሲስ ከንፈ ገብርኤል አለታዬ ጋር ውይይት አድርገን የሚከተለውን አጭር ማብራሪያ አግኝተናል ።

ከሁለቱ ባለሥልጣኖች እንደተረዳነው በአሁኑ ጊዜ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥር ጥንታዊና ዘመናዊ ተብለው የሚጠሩ ሁለት ዓይነት ት/ቤቶች አሉ ። ጥንታዊ ተብለው የሚጠሩት ት/ቤቶች በየገዳማቱና በየአድባራቱ የሚገኙት ከሠራዊተ ፊደል ጀምሮ ፀዋትወ ዜማ ፤ ቅኔ ፤ አቋቋምና ትርጓሜ መጻሕፍት የሚሰጥባቸው ናቸው። ከብዙ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ደብረ ሊባኖስ ደብረ ጽጌ ፤ ታዕካ ነገሥት በዓታ፤ ዋሸራ ቤተ ልሔም ዙር አባ ፤ ጐንደር በዓታ ግምጃ ቤት ማርያም አክሱም ጽዮን ሰለል ኩላ ፤ ደብረ ዓባይ፤ ደብረ ቢዘን የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል ።

ዘመናዊ ት/ቤቶች የሚባሉት የአካባቢውን ኅብረተሰብ ለመርዳት ታስቦ በአማካይ ቦታ የተሠሩ ት/ቤቶች ናቸው ። የእነዚህ ት/ቤቶች ፕሮግራም የሚመራው ትምህርት ሚ/ር በሚያወጣው የትምህርት መመሪያ ነው በነዚህ ት/ቤቶች ቤተ ክርስቲያኗ የሃይማኖት ትምህርት በተጨማሪ ታስተምራለች ።

በአሁኑ ጊዜ ምን ያህል ት/ቤቶችና መምህራን እንዳሉ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ ያገኘነው የጽሑፍ ማስረጃ የሚከተለውን አኃዝ ያሳያል ።

የጥንታዊ ት/ቤቶች ብዛት ፩፻፭፩
» መምህራንና ሠራተኞች ብዛት ፩፹፫፻፴፯
በትሩፋት ት/ የሚሰጥባቸው ቦታዎች ፱፻፭፬
በትሩፋት ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን ብዛት ፱፻፭፬
የዘመናዊ ት/ቤቶች ብዛት ፴፭

በጠቅላይ ቤተ ክህነት ከትምህርትና ማሰልጠኛ መምሪያ ኃላፊዎች ጋር ባደረግነው ውይይት በመምሪያው በኩል አንድ አንድ ቅሬታዎች እንዳሉ ገልጸውልናል ።

እነርሱም ሀ/ ለትምህርት የተመደበ በቂ በጀት የለንም

ለ/ የመምሪያው ስም የትምህርትና ማሠልጠኛ ሁኖ ሳለ የማሠልጠኛው ሥራ ለእኛ አልተሰጠም ።

ሐ/ የነፃ ትምህርቱ (ስኮላር ሽፕ) ኃላፊነት በእኛ በኩል መሆን እንዳለበት የተሰጠን መመሪያ ይገልጣል ነገር ግን ኃላፊነቱ ከእኛ ቁጥጥር ውጭ ነው ።

መ/ ትምህርትን በሚመለከት ጉዳይ ብዙ ጊዜ ሪፖርት እያቀረብን በሥራ ላይ ሳይውልልን ቆይቷል የሚሉ ነጥቦች አሉበት ።

ቢሆንም የሚመራ ክፍል የተሰጠውን መመሪያ ተከትሎ የማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመጠቆም እንወዳለን ከመደበኛ ት/ቤቶች ሌላ የኢትዮጵያ ኦ-ተ-ቤ-ክ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት በምታገኘው እርዳታ አምስት የካህናት ማሠልጠኛዎች ከፍታ በማስተማር ላይ ትገኛለች ። እነዚህ ማሠልጠኛዎች የ፲፩ቱን አህጉረ ስብከት ካህናት እንዲያገለግሉ ተብሎ በጥናት የተከፈቱ ናቸው ። የማሠልጠኛዎቹ ማዕከል የሚከተሉት ናቸው ።

፩- በዝዋይ ሐይቅ ዳር የሸዋ የሐረርጌና የአርሲ ካህናት

፪- በአዋሳ ሐይቅ ዳር የሲዳሞ የባሌና የጋሞ ጐፋ ካህናት

፫- በቡኖ በደሌ የኢሉባቦር የከፋና የወለጋ ካህናት

፬/ በባሕር ዳር የጐጃምና የጐንደር ካህናት

፭- በመቀሌ የትግራይ የወሎና የኤርትራ ካህናት በስብከት ዘዴ ፤ በእርሻና በተግባረ ዕድ ሙያ በየጊዜው እየሠለጠኑ ነው ።

በነዚህ ማሠልጠኛዎች የሚሠለጥኑት ካህናት ከሥራ መደባቸው ላይ እየተመለመሉ ስለሚመጡ ትምህርቱ ተግባራዊ ነው ማለት ይቻላል በተጨማሪም ካህናቱ ከተለያዩ ቦታዎች ስለሚመጡ አንዱ ከሌላው የሚያገኘው የሥራ ልምድ እጅግ ጠቃሚ ነው ።



መምሁሩ ተማሪቹን ሰብስበው ያስተምራሉ ፤

ለቤተ ክርስቲያኗ ታላቅ የዕውቀት መድበልና የምሁራን መፍለቂያ ይሆናል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት በኢት/ ኦ.ቤ.ክ.ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በአዲስ አበባ በቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት የተከፈተው ከፍተኛ ት/ ቤት ነው ። ይህ ት/ቤት በ፲፱፻፸፬ዓ.ም. ሥራውን ጀምሮአል ትምህርት ቤቱ ደረጃውን ጠብቆ የሚፈለግበትን ዓላማ እንዲፈጽም ምዕመናን በገንዘባቸው ካህናት በጸሎታቸው እንዲረዱት ያስፈልጋል ።

# ክርስቲያኖች የትንሣኤን በዓል ለምን . . .

ከ፰ኛው ገጽ የዞረ

በኋላ የ፲፫ ቀኖች ልዩነት አለው በማለት ሌላ ሦስተኛ ማስተካከያ ስላወጣ ይህን የተቀበሉ ሁሉ ከጎርጎርዮስ የቀን መቁጠሪያ ስለተለዩ የትንሣኤ በዓል በሦስት የተለያዩ ቀናት መከበር ተጀመረ ።

ይኸም በ፲፱፻፳፫ ዓ-ም የተደረገው ማስተካከያ በየ፬ ሺህ ዓመት አንድ ቀን እንደሚተርፍ ተደርጎ ተቀመረ ተባለ እንጂ አሁንም ካሌንደሩ ከስህተት ለመዳን ፍጹምነትን አላገኘም ።

እነሆ በዚህ መልክ የጥንቱ ሥርዓት ስለተሻረ እንደ ጁሊየስ፣ እንደጎርጎርዮስ፣ እ/ኤ/አ/ እንደ ቁስጥንጥንያ አቆጣጠር በሚባለው ልዩነት ምእመናን ግራ ተጋብተው የትንሣኤን በዓል በተለያዩ ዕለታት ማክበር ግድ ሆኖባቸው ያም የኔ ነው ጥሩ ያም የኔ ነው ትክክል ሲባባሉ መዘበቻ ሆነው ይታያሉ ።

ጥንታውያን የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን የሚከተሉት የኒቅያን ጉባኤ ውሳኔ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን የቀን አቆጣጠራቸውና የበዓላት አቀማመራቸው አሁንም የጥንቱን የተከተለ ነው ። ካሌንደሩም ተስተካክሎ ፍጹምነትን ለማግኘት ካልቻለ ለአብያተ ክርስቲያናቱ አንድነት የሚሻለው የጥንቱን ተከትሎ ማክበሩ ነበር ።

ግን ከላይ እንደጠቀስኩት ልዩነቱ ከአብያተ ክርስቲያናቱ ማን ከማን ያንሣል በሚል መንፈስ የተሠነዘረ ስለሚመስል ተለያይቶ የትንሣኤን በዓል ማክበሩ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ማመዘኑን ማንም ሊገነዘበው ይችላል ።

መቸም በሃይማኖት በኩል ከተመለከትነው ቁም ነገሩ የትንሣኤን በዓል ታላቅነት ተረድቶ የድኅነት ዓርማ የእምነት ሰንደቅ ዓላማ መሆኑን አውቆ ማክበሩ ነው ።

ይህንም ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ገልጦታል ። «ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያውስ ስብከታችን ከንቱ ነው ። እምነታችንም ደግሞ ከንቱ ናት» ። ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፭ ፲፬ ። ለክርስቲያኖች ሁሉ ትልቅ

ተከታዩ ወደ፰ኛው ገጽ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከትምህርተ ወንጌል ጋር የልማት ተግባሮችንም በሰፊው እየዘረጋች እንድትሠራ ቅዱስ ሲኖዶስ መመሪያ አውጥቶ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማስተላለፉ የሚታወስ ነው ።

ከቅዱስ ሲኖዶስ የተላለፈውን መመሪያ መሠረት በማድረግ የሰበካ ጉባኤ አባላት የሆኑ ሁሉ እያንዳንዳቸው ከሕዝበ ክርስቲያኑና ከካህናቱ ጋር በመተባበር በየአብያተ ክርስቲያኑ አጥቢያ የልማት አውታሮችን በመዘርጋት ካህናት የትርፍ ጊዜያቸውን በልማት ሥራ ላይ እንዲያውሉት ለማድረግ በመጣር ላይ ይገኛሉ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለልማት ተግባር እንግዳ አለመሆኗ ቢታወቅም በይበልጥ በአሁኑ ጊዜ በየአብያተ ክርስቲያኑ አጥቢያ የሚቋቋሙት የልማት ተግባሮች በርከት እያሉ ሄደዋል የተቋቋሙትና ለወደፊትም የሚቋቋሙት የቤተ ክርስቲያን ልማቶች ሁሉ ለቤተ ክርስቲያናችን ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ አንጠራጠርም።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር ተቋቁመው የልማት ተግባሮችን በንቃትና በትጋት ከሚያከናውኑት ድርጅቶችም አንዱ የጐፋ ቅዱስ ገብርኤል ተግባረ እድ ማሠልጠኛ ት/ቤት ነው ይኸው ድርጅት የሚያከናውናቸው የልማት ተግባሮች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈሉ ሲሆን እነርሱም ፤—

፩— የብረታ ብረት
፪— የሽመና
፫— የእንጨት
፬— የሽያጭ ክፍሎች ናቸው

የብረታ ብረቱ ክፍል የብረት መዝጊያዎችንና መስኮቶችን ፤ ካዝናዎችን፤ የብረት አልጋዎችን ፤ ለወንበሮች ፤ ለቁም ሳጥኖች ፤ ለጠረቤዛዎችና ለኮመዲናዎች የሚያገለግሉ ብረታ ብረቶችን እያዘጋጀ ያቀርባል ።

የእንጨት ሥራው ክፍል ጠረቤዛዎችን ፤ ወንበሮችን ፤ ቁም ሳጥኖችን፤ አልጋዎችን ፤ ኮመዲናዎችን ፤ መዝጊያዎችን ፤ በጠረቤዛ ላይ የሚቀመጡና በእጅ የሚያዙ መስቀሎችን የሚታጠፉና የሚዘረጉ የእንጨት ቅርጽ የሆኑ ሥዕሎችን ፤ ታጣፊና ተሽከርካሪ ወንበሮችን ፤ የሸራ አልጋዎችን ፤ መንበሮችንና የመሳሰሉትንም ይሠራል ።



አቶ ገብረ ሚካኤል ድፈር ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ፤

የሽመና ክፍሉ ደግሞ ለመጋረጃና ለፎቴ የሚያገለግሉ ጨርቆችን ፤ ልብሶችን ጋቢዎችንና የመሳሰሉትን እየሠራ ያቀርባል ።

የሽያጭ ክፍሉ ከተጠቀሱት ክፍሎች እየተዘጋጁ የሚቀርቡለትን ዕቃዎች እየተቀበለ የሚሸጡበትን ዋጋ በመተመን ለመግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች ይሸጣል ።

ወንበር ፤ ጠረቤዛ ፤ ቁም ሣጥን ፎቴና የመሳሰሉትን ለማሳደስ ለሚፈልጉም ሰዎች ድርጅቱ አስቀድሞ ሠራተኞችን በመላክ ለእድሳት የሚያስፈልገውን ዕቃና ዋጋ ካስተመነ በኋላ በማደስ አገልግሎቱን ለኅብረተሰቡ ያበረክታል ።

ስለድርጅቱ ያስረዱን ዘንድ የዚህኑ ጥበበ እድና ማሠልጠኛ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ገብረ ሚካኤል ድፈርን ጠይቀናቸው ሲያብራሩ ድርጅቱ የተቋቋመው ቀደም ብሎ መሆኑ ቢታወቅም ሥራውን በሚገባ እያጠናከረ መሥራት የጀመረው ከ፲፱፻፷፱ ዓ·ም ወዲህ ነው ድርጅቱ ሥራውን የሚያከናውነውም በአራት ክፍሎች ክፍሎ ሲሆን በየክፍሉ የተመደቡትም ሠራተኞች በንቃትና በትጋት ሥራቸውን ይሠራሉ፤ነገር ግን የተግባረ እድ ውጤቶች የሆኑትን ዕቃዎች ለሚፈልጉ ሰዎች በወቅቱ የምናቀርብበት የመሸጫ ሱቅ የለንም ፤ ከዚህ የተነሣ ዕቃዎቹ ሁሉ ተሠርተው ሲያበቁ ሳይሸጡ በዚሁ የሽያጭ ክፍል ለብዙ ጊዜ መቆመጥ ግድ ይሆንባቸዋል ለጉብኝት የመጡ ወይም የሚያውቁ ሰዎች መጥተው ካልገዙን በስተቀር ገበያ አውጥተን ለመሸጥ አንችልም ካሉ በኋላ አቶ ገብረ ሚካኤል ማብራሪያቸውን በመቀጠል ።

ጠቅላይ ቤተ ክህነት በጉዳዩ አስቦበት ከዚህ የሚመረቱትን ዕቃዎች እየተቀበለ እንዲሸጡ ቢያደርግ ወይም የመሸጫ ሱቅ ቢሰጠን የምርታችን ውጤት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ እንደሚሄድ አንጠራጠርም ዋናው ችግራችን ግን ይኸው የመሸጫ ቦታ ያጣት ነው ብለዋል ።


በድርጅቱ የሚቀጠሩት ሠራተኞች ምንና ምን ያሟሉ መሆን አለባቸው ? ለሚለውም ጥያቄ ሥራ አስኪያጁ ሲመልሱ ድርጅቱ ማሠልጠኛ ስለሆነ ለመሠልጠን የሚፈልጉትን ሰዎች ይቀበላል እንጂ የሠለጠኑትን ተቀብሎ በቀዋሚነት አይቀጥርም ለማሠልጠን የሚቀበላቸው ሰዎችም ከሰበካ ጉባኤ እንዲሠለጥኑ የተፈቀደላቸው መሆኑን የሚያስረዳ ደብዳቤ ማምጣት አለባቸው ደብዳቤ ይዘው ከመጡ ድርጅቱ ተቀብሎ እንዲሠለጥኑ ያደርጋል በማለት ተናግረዋል ።

ድርጅቱ ለወደፊቱ ስላለው ዕቅድ አቶ ገብረ ሚካኤል ድፈር ተጠይቀው ሲያብራሩ ድርጅቱ ከአሁን በበለጠ ሥራውን አስፋፍቶ ለመሥራት ከፍ ያለ ዕቅድ አለው ። ይህ ድርጅት ከ፲፱፻፷፱ ዓ.ም.ጀምሮ እስከ ፲፱፻፸፬ የካቲት ወር ድረስ ከዋናው ቤተ ክህነት ጋር ሳይዋሃድ በገለልተኛነት ሥራውን ሲሠራ ቆይቶ ነበር ከየካቲት ፲፭ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ወዲህ ግን በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥር ሆኖ ተግባሩን እንዲያከናውን ተወስኗል ይህም በመሆኑ ከቀድሞው የበለጠ የሥራ እንቅስቃሴ እያሳየ ነው የሥራውንም ውጤት በማሳደግ ላይ ይገኛል ወደፊትም ከአሁን በበለጠ ሥራውን አስፋፍቶ ለመሥራት ሰፋ ያለ ዕቅድ አለው ፤ በተጨማሪም ድርጅቱ ማሠልጠኛና ማምረቻ እንደመሆኑ መጠን ወደፊት የሚሠለጥኑትንም ሰዎች ቁጥር ከፍ በማድረግ በርከት ያሉ ሠልጣኞችን ተቀብሎ ለማሠልጠን አስቧል ብለዋል ።

ከአሁን ቀደም ድርጅቱ ስለአሠለጠናቸውና አሁን ስለሚሠለጥኑት ተጠይቀው ሲያስረዱ ከአሁን ቀደም ከ፫፻፶ ያላነሱ ሰዎችን ያሠለጠነ ሲሆን ሁለት ሰዎች ደግሞ በመሠልጠን ላይ ይገኛሉ ። እነርሱም ከክርስቲያን ተራድኦ ድርጅት የተላኩ ናቸው ሲሉ አስረድተዋል ።

በተጨማሪም አቶ ገብረ ሚካኤል ድፈር ሲናገሩ ድርጅቱ የቆዳ ስፌት መኪና ለማቋቋም በመጣር ላይ ይገኛል የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ የድርጅቱም ዓላማ ተሳክቶ በተቋቋመ ጊዜ የምርቱን ውጤት በእጥፍ ሊያሳድገው እንደሚችል አንጠራጠርም ብለዋል።

እንዲሁም ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በቅጽረ ግቢው መኖሪያቸውን አድርገው የመሥሪያ ቤቱን ቁልፍ የሚይይዙትንና የጽዳት ሐላፊ የሆኑትን አባ ፈለቀ እሸቱን ስፌት ሲሰፉ ተመልክተን አነጋግረናቸው ነበር ፤— አባ ወደዚህ ድርጅት ከመምጣታቸው በፊት በደብረ ሊባኖስ ገዳም ለ፳ ዓመታት ቆይተው ከ፲፱፻፷፱ ዓ·ም ወዲህ ግን በጐፋ ቅዱስ ገብርኤል እደ ጥበብ ማሠልጠኛ ግቢ እንደሚኖሩ አስረድተውናል ።



የዕደ ጥበቡ ማሠልጠኛ ት/ ቤት ሥራውን የሚያከናውነው በዚህ መልክ ነው ።

አባ ፈለቀ እሸቱ ሥራ መፍታትን አይወዱም ከሥራ ወዳድነታቸው የተነሣ በትርፍ ጊዜያቸው ልዩ ልዩ ተግባረ እዶችን ይሠራሉ ከሚሠሯቸውም ሥራዎች አንዱ ስፌት እየሰፉ መሸጥ ነው ፤ አባ አገልግሎችን ፤ ሰፌዶችንና የመሳሰሉትንም እየሰፉ ይሸጣሉ ከሚሰፏቸውም አገልግሎች አንዱ አገልግል ብር ፴፭ ድረስ እንደሚሸጥ አስረድተውናል ለስፌት የሚጠቀሙባቸውን አከርማዎችና ሰበዞችንም በወቅቱ በዚያው አካባቢ እንደሚቀጩአቸው አስረድተውናል በተጨማሪም አባ ፈለቀ በመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ልዩ ልዩ አትክልቶችን በመት

ተከታዩ ወደ፲፮ኛው ገጽ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ሐዋርያዊ ትእዛዝ

የሰው ዘር በምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ነቢዩ ሙሴ ድረስ ሰዎች ሁሉ በሕገ ልቡና እየተመሩ ጠቃሚውን ከሚጐዳ መልካሙን ከክፉ ለይተው ያውቁና ይሠሩ ነበር ። በሕገ ልቡና እየተመሩ ሥነ ፍጥረትን እያስተዋሉ ሀልዎተ እግዚአብሔርን የተረዱ የአበው ትምህርት ተጨማሪ መመሪያ እየሆነ ለአማኞች በሙሴ አማካይነት የተሰጠው ሕግ መጽሐፋዊ እስከ ተገኘ ድረስ ሰዎችን ሁሉ ከክፋት ወደ በጐነት ከጥፋት ወደ ልማት ሲመራ ቆይቶአል ።

በሙሴ አማካይነት ለብሉይ ኪዳን አማኞች የተሰጠው ሕግም በሰዎች መካከል የእርስ በርስ መገዳደል እንዳይኖር ፤ አንዱ የሌላውን ገንዘብ እንዳይነጥቅ ፤ ሰው ሁሉ የባልንጀራው የሆነውን መልካም ነገር ሁሉ ለራሱ ለማድረግ እንዳይመኝ ማንኛውም ሰው በባልንጀራው ላይ የሐሰት ምስክር እንዳይሆን ያስተምር ስለነበር ለመንፈሳዊ ሕይወትና ለማኅበራዊ ኑሮ ከፍተኛ አገልግሎት ሰጥቶአል ዛሬም እየሰጠ ነው ።

በኋላም የዓለም መድኀን ክርስቶስ «አትግደል» የሚለውን «አታስቆጣ» በሚለው አታመንዝር የሚለውን አትመኝ» በሚለው ሕግ ፍጹም አድርጎ አስተምሮአል ። ከእርሱ ተምረው ወንጌልን ያስተማሩ ሐዋርያትም ለአስተማሩአቸው ምእመናንና በየጊዜው ለሚነሡ የወንጌል አማኞች ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚያደርግ ከክፉ ነገር የሚከለክል ትእዛዝ ሰጥተዋል ።

ትእዛዙ ወይም ትምህርቱ እንዲህ ነው «ሁለት ሐሳብ አይኑርህ በሁለት ምላስ አትናገር ሁለት ምላስ ወደሞት የሚያደርስ ወጥመድ ነው ያዕ-፫-፮—፱ ቃልህ ሥራን የሚፈጽም ይሁን እንጂ ሐሰት ወይም ከንቱ አይሁን የሌላውን ገንዘብ አትመኝ አጭበርባሪ ወይም ግብዝ አትሁን ተንኰለኛ ወይም ኩራተኛ አትሁን በጎረቤትህ ላይ ክፋትን አታስብ ። —— የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምርህን በቀንና በሌሊት አስበው ጌታንም እንደምታከብረው አክብረው ሰዎች የጌታን ነገር ሲነጋገሩ ጌታ ከዚያ አለና»

ከክፉ ጋር የዋለ ክፉ ፤ ከደግ ጋር የዋለ ደግ እንደሚሆን በፍርድ ማድላትና ወላዋይ መሆን እንደማይገባም ትምህርቱ እንዲህ ይላል «የቅዱሳንን ቃሎች ሰምተህ እንድትማር ዕለት ዕለት ወደ አሉበት ተጠጋ ። ጠብ አትፍጠር የተጣሉትን አስታርቅ በጽድቅ ፍረድ ለሰው ፊት ሳታደላ ስለ ስሕተቱ ገስጸው ። ልብልን ? ልተወው ? [illegible] «ማንነትህን እንዳውቀው ጓደኛህን ንገረኝ» የሚል አነጋገር አለ ከቅዱሳን ጋር የዋለ ቅዱስ ከኃጥእ ጋር የዋለም ኃጥእ መሆኑ ነው ፊት አይቶ ሳያዳሉ መፍረድና የተጣሉትን ማስታረቅም የእግዚአብሔር ልጅ የሚያሰኝ ዐቢይ ቁም ነገር ነው ። ሊሆን የሚገባውን ያለማመንታት በቆራጥነት በጊዜው ማድረግም ደጋግ ሥራዎች ሁሉ ሊከናወኑ የሚችሉበት ታላቅ ጉዳይ ነው ።

የተቸገሩትን ስለመርዳትና ያለውን ለሌለው ማካፈል እንደሚገባም እንዲህ ታዝዞአል ሳትጠራጠርና ሳታጉረመርም ስጥ መልካሙን ዋጋ የሚሰጥ ማን መሆኑን ታውቃለህና ያጣውን አታባርር ያለህን ሁሉ ለወንድምህ አካፍለው።

ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ሠራተኞችንም በግብረ ገብነትና በሥነ ሥርዓት በርህራሄ ማሳደግና ማስተዳደር እንደሚገባ ሲያስረዳ «ወንድ ወይም ሴት ልጅህን ከመቅጣት እጅህን አትመልስ ከሕፃንነት ጀምሮ እግዚአብሔርን በመፍራት አሳድጋቸው ። ከአንተ ጋር ሁነው በአንድ እግዚአብሔር ተስፋ የሚያደርጉትን ሠራተኞች በቁጣህ አትዘዛቸው ያለዚያ የሁለታችሁንም አምላክ ሳይፈሩ ይቀራሉ እርሱም በመንፈስ የተዘጋጁትን እንጂ ፊታቸውን ተመልክቶ ሊጠራቸው አልመጣም» በማለት ወላጆችንና የቤተ ሰብእ ኃላፊዎችን ይመክራል ።

ምእመናንን ስለሚያስተምሩ እውነተኞች መምህራንና በትምህርተ ወንጌል እያመካኙ ያለ ሥራ በሰው ድካም ለመኖር ስለሚፈልጉ ባሕታውያን መሰል ሰዎችም «ከዚህ ቀደም የተነገረውን ትምህርት (የወንጌል ትምህርት የሚያስተምራችሁ ሰው ቢኖር በደስታ ተቀበሉት ። ግን ዞሮ አጥፊ የሆነ ሌላ ትምህርትን ቢያስተምር አትስሙት ጽድቅንና የጌታን ዕውቀት የሚያንጽ ከሆነ ግን ጌታን እንደምትቀበሉ በደስታ ተቀበሉት ።

ስለ ሐዋርያትና ስለነቢያት ስለ ካህናትና መምህራን እንደ ወንጌል ትእዛዝ እንዲሁ አድርጉ ወደ እናንተ የሚመጣውን ሐዋርያ ሁሉ ጌታን እንደምትቀበሉ ተቀበሉት ነገር ግን በእንግድነት አንድ ቀን ብቻ ይቀመጥ ቢያስፈልግም ሁለት ቀን ይደር ። ሦስተኛ ቀን ቢቀመጥ ግን ሐሰተኛ (ሥራ ፈት) ሐዋርያ ነው ።

በመንፈስ የሚናገር (የሚያስተምር) ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር ስጠኝ ቢል አትስሙት ለተቸገረ ስጡ ቢል ግን

ተከታዩ ወደ፲፰ኛው ገጽ ዞሯል



# የግብርና በረከት

ግብርና በማንኛውም ክፍለ ዓለም የኢኮኖሚ ዕድገት ዋልታ ፤ የሰው ሕይወት መሰላል ነው ። በጉልህ እንደሚታወቀው በዓለም ከሌላው ላቅ ብለው የሚታዩ ኃያላን መንግሥታት አሁን ካሉበት የዕድገት ደረጃ ለመድረስ የበቁት የየአገራቸውን የእርሻ አቅዋም ለማሻሻል ባደረጉት ጥረትና ባገኙት የግብርና በረከት መሆኑን እንረዳለን ።

እዎ የአንድን አገር የእርሻ ውጤቶች በሚገባ ለመጠቀምና የተዛመዱ የእርሻ ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም አዳጋች አይሆንም ነገር ግን በማንኛውም ጊዜና ቦታ የእርሻ ሥራን ለማቋቋም ሲፈለግ የአራሹን ጥበብና ዕውቀት ከተሰማሚው የእርሻ ቦታ ላይ አውሎ የተፈለገውን የሰብል ዓይነት በተገቢው ሁኔታ ማምረት ያስፈልጋል ።

የግብርና ሥራ የተፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው አራሹ በተፈጥሮም ሆነ በሳይንስ የእርሻ አጠቃቀም ዘዴ የሚበቅለውን የእህል ዓይነት በትሰማሚው ቦታ ዘርቶ ከዘር እስከ መከር ሊያገኝና ሊያስገኝ ሲችል ነው።

ከዚህም ጋር አራሹ ያገኘውን የምርት ውጤት በደኅና ዋጋ ሽጦ በዚህ ሥራ ያወጣውን የጉልበት ፤ የዕውቀትና የማቴሪያል ድምር ወጭውን ሸፍኖ የዕለት ፍላጎቱን ለማሟላት የበቃ እንደሆነ ነው ።

እርሻን ቋሚ ሥራው ያደረገ አንድ አራሽ ገበሬ በየጊዜው የሚደረጉ የእርሻ ነክ ለውጦችን እንደየአስፈላጊነታቸው አምኖ በመቀበልና ከሥራ ላይ አውሎ በግብርና በረከት በይበልጥ ለመጠቀም ምንጊዜም ከፍላጎት ጋራ ዝግጁ ሆኖ መገኘት አለበት ።

ዓላማው በእርሻ አቅዋም ላይ የተመሠረተ ከሆነ የሚገለገልባቸው የእርሻ መሣሪያዎችና ስለ እርሻ አጠቃቀም የወጡ መመሪያዎች ሁሉ የበለጠ ጥቅም እየሰጡና የበለጠም እንክብካቤ እያገኙ እንዲሄዱ ያደርጋል መሣሪያዎቹም እንክብካቤ አግኝተዋልና ያለችግር እንደሚጠቀምባቸው አያጠራጥርም ።

አንዳንድ የኢኮኖሚ ዕድገት ጠበብቶች ሲተቹ «ገና በማደግ ላይ ያሉና የዕድገት ደረጃቸው ዝቅ ብሎ በሚገኙ አገሮች የእርሻ ሥራ የአንድ አገር የገቢ ምንጭ ከመሆኑም በላይ ለብዙ ሕዝብ መተዳደሪያ ሆኖ ይታያል » ይላሉ የእርሻ ሥራ በጥንታዊነቱ ከሌሎች ሥራዎች ሁሉ በልጦ የተለመደና የታወቀ በመሆኑ በሌላው የሥራ ዘርፍ ከሚሰማራው ሠራተኛ ይልቅ በእርሻ ሥራ የተሰማራው ሕዝብ ቁጥር ከፍ ብሎ ይገኛል። ይህ በመሆኑም በሌላው ሥራ ተሰማርቶ የሚሠራው ሠራተኛ በግብርና በረከት ተደስቶ ሥራውን ያለችግር ሲያካሂድ ይገኛል ።

ዘመን ዘመንን ሲተካ ፤ ሳይንስ የበለጠ እያደገና ከምን ጊዜውም እየረቀቀ በመጣ ቁጥር ባልተለመደና ባልተሠራበት የሥራ ዘርፍ በመሰማራት የኅብረተ ሰቡን ፍላጎት ሠርቶ ለሟሟላት ፈቃደኞች የሆኑ የሳይንስ ጠበብቶች በየጊዜው መውጣታቸው ቢታወቅም ኅብረተሰቡ ይህን የማኅበራዊ ደረጃቸውን ዝቅ አድርጎ እያየና አስፈላጊነታቸውን በይበልጥ ለመረዳት ባለመቻሉ የጥበበ ዕድ ሥራቸውን አስፋፍተው ለእርሻ አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑ አዳዲስ ዕቃዎችን ሠርቶ ለማቅረብ አይደፍሩም የሚያበረታታቸው አይገኝምና በዚህ ምክንያት ገበሬው ቀደም ሲል በተለመዱት የእርሻ መሣሪያዎች ሲሠራ ቆይቶአል ።

በዚህ አሠራር ልሥራ ማለት ደግሞ የኢኮኖሚ ዕድገት ዋልታ የሆነውን የግብርና ሥራ ጨርሶ ማመንመን ሆኖ በመገኘቱ ለእርሻ አገልግሎት የሚጠቅሙ እጅግ በጣም በረቀቀ ፍልስፍና የተሠሩ መሣሪያዎች ለአገልግሎት ቀርበዋል ። ለረጅም ጊዜ አሠራራቸውና ቅርፃቸው ሳይለወጥ የተጠቀምንባቸው የእርሻ መሣሪያዎች ሙሉ በሙሉ ያልቀሩ ቢሆንም ዛሬ ዓለም በእርሻ ሥራ በዘመናዊ መሣሪያዎች እየተጠቀሙ በዚህ ሥራ ወደ ኋላ የቀሩትን አገሮች እየመገበ ይገኛል ።


እዎ አንድ ሰው ምንጊዜም ቢሆን ለዕለት ፍላጎቱ የሚሆኑትን መሣሪያዎች ራሱ ብቻ ሠርቶ ሊገለገል እንደማይችል ግልጽ ነው ፤ ይህ ከሆነ ዘንድ አራሹ ገበሬ ባለጁን ፤ አናጢውን ፤ አንጥረኛውን ፤ ቆዳ ፋቂውንና የመሳሰሉትን አገልግሎት ሰጭ ባለሙያዎችን ሊንቅ አይገባውም ። ምክንያቱም ገበሬው አናጢ ፤ አንጥረኛ ባለጅ ሆኖ ሊሠራ ቢሞክር የሚያገኘው የሥራ ፍሬ ለራሱ ብቻ ሆኖ ቢቀር እንጂ አተረፍርፎ ሠርቶ ከሁሉም ዓይነት ለሽያጭ ወደገበያ ማቅረብ አይችልም ስለዚህ የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብር በፈጠራ በተገኙ መሣሪያዎች ሁሉም እንዲጠቀም ለማድረግ እያንዳንዱ ገበሬ በየፊናው የሚሠሩትን የግብርና መሣሪያዎች በየግንባሩ ለገበያ ቢያቀርብ እንዲለዋወጥ ይረዳዋል ይህ ዓይነቱ የሥራ ክንውን ሠራተኛውን ለጥበበ ዕድ ከማደርጀቱም በላይ የሥራው ውጤት ተፈላጊነት እያገኘ የእርሻ ሥራ በበለጠ ተጠናክሮና ዳብሮ የአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት የታቀደውን ግብ ሊመታ ይችላል ።

ወደ አገራችን ገባ ብለን የእርሻን አቅዋም የተመለከትን እንደሆነ ከጥቂት ዓመታት ቀደም ሲል በነበረውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከተደረጉት



www.ethiopianorthodox.org

የእርሻ ለውጦች መካከል ብዙ ልዩነ ቶችን ማየት ይቻላል ፤ ቀደም ሲል የእርሻ መሣሪያውም ሆነ የአስተራረስ ዘዴው ጥንታዊ በመሆኑ የማረሻው ዓይነትና የገበሬ ዕቃው በመጠኑና በክ ብደቱ አነስተኛ በመሆኑ በየዓመቱ የሚታረሰው እርሻና የሚከሰከሰው አፈር ከተወሰነው ጥልቀት በታች እያ ልፍም ። የሚዘሩትም የሰብል ዓይነቶች



ካህናቱ በልማቱ ተግባር ተሠልፈው ሲሠሩ ፤

አበቃቀላቸው የሚመሠረተው በለስ ለሰው አፈር ላይ በመሆኑ በየጊዜው የሚጠቀሙባቸው አስፈላጊ ንጥረ ነገሮች በሚፈለገው መጠን ባለመ ገኘታቸው የአዝርዕትን ዕድገት ሊቀ ንሱ ይችላሉ የአዝርዕቱ ዕድገት በተ መጣጣኝ ሁኔታ ሳይሳካ ሲቀር የም ርቱም መጠን ከመቀነሱም በላይ በገበያ ተፈላጊነት ያለው ጥሩ ዓይነት ሰብል ለማቅረብ አዳጋች ይሆናል ።

በአገራችን ተለምዶ እንደቆየው ገበሬው የሚጠቀምበት የዘር ዓይነት ካመረተው ምርት ከፍሎ ለዘር በማ ስቀመጥና በመዝራት ስለሆነ በሚፈ ለገው የዘር አስተዳደግ ሥነ ሥርዓትና የተመጠነ የዕድገት ጊዜ ውስጥ በቅሎ አብቦና አሽቶ ባለመብሰሉ ምክንያት የተጠበቀውን ያህል ምርት ላይሰጠው ይችላል ፤ ዘሩም ያልተመረጠ በመሆኑ ከውስጡ አብሮ ያለው አረም አብሮ ስለሚበቅል የገበሬው ድካም ፍሬ አልባ ሆኖ ይቀራል ።

ስለዚህ አራሹ ገበሬ በሥራው ንቃ ትና ትጋት ፤ የዘር አመራረጥን ፤ የአ ስተራረስ ልምድና የአጠቃቀሙን ዘዴ ማወቅ ይኖርበታል ።

ክርስቶስ የእርሻን ክቡርነት አስ መልክቶ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ሲያስተምር «ዘሪ ሊዘራ ወጣ ሲዘራም አንዱ በመንገድ ዳር ፤ ሌላው በጭንጫ ላይ ሌላው በሾህ መካከል ሌላው ግን በለሰለሰ መሬት ላይ ወደቀ » ከሁሉም በላይ በለሰለሰው መሬት ላይ የተዘራው አንዱ መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሰላሳ ፍሬ እንደሰጠ አስገንዝቦአል ማቴ ፲፫ ቁ- ፫—፱

አሁንም እርሻን መደበኛ ሥራ አድ ርጐ የተሰማራ ገበሬ ስለእርሻ አጠቃ ቀም የወጡ ዘመናውያን መሣሪያዎችን በተግባር ቢተረጉም የድካሙን ውጤት አግኝቶ በርሱ ድካም ውጤት የሚጠ ቀሙ ወገኖችንም በሥራ ፍሬው ሊያ ስደስት ይችላል ገበሬ የዓለም ሕዝብ መጋቢ ነውና ።

ከእርሻ ምሁር የተገኘ
አትራቢ በለጠ አበበ

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ከ፲፫ኛው ገጽ የዞረ

ከል ይጠቀማሉ አባ ለሰነፎች መል ካም ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ትጉህ መነኩሴ ናቸው ሥራ ፈትነት የሰውን ልጅ ከከባድ ስሕተት ላይ ይጥላል ስለ ዚህ እንደ አባ ፈለቀ እሸቱ የትርፍ ጊዜን በሥራ ላይ ማዋል ከስሕተት የሚጠብቅ ከድንቁርናና ከረኃብ የሚ ያላቅቅ ፍቱን መድኃኒት ስለሆነ ሁሉም ሰው የትርፍ ጊዜውን በቁም ነገር ሥራ ላይ ማዋል እንዳለበት ሊገነዘበው ይገ ባል ።

የጐፋ ቅዱስ ገብርኤል እደ ጥበብ ማሠልጠኛ በሦስት ክፍሎች በመክ ፈል የሚሠራቸው የሥራ ውጤቶች ሁሉ ለቤተ ክርስቲያናችን አለኝታ ዎች ናቸው ። ነገር ግን ዕቃዎቹ እየተ ሠሩ ለተጠቃሚው ሕዝብ የሚቀርቡ በት ሱቅ ባለመኖሩ ተሠርተው ሳይ ሸጡ ለብዙ ጊዜ እንደሚቆዩ ዋና ሥራ አስኪያጁ አስረድተውናል ። ይህም ሊታሰብበት የሚገባ ዓቢይ ጉዳይ ስለ ሆነ የሚመለከተው ክፍል ለዚሁ ተግ ባር ዋና ትኩረት በመስጠት ተሠር ተው የሚወጡት የተግባረ እድ ውጤ ቶች የሚሸጡበት ሱቅ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት ።

አብያተ ክርስቲያናትም ቢሆኑ በዚሁ ድርጅት ውስጥ የሚሠሩትን ዕቃዎች እየገዙ እንዲጠቀሙ በዚህ አጋጣሚ መንፈሳዊ መልእክታችን እናስተላልፋለን ።

ቄ- ልሣነ ወርቅ በዛብህ



# «የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት»

መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንቀ በለው ? የጻፈውስ ማን ነው ? ሰው ወይስ እግዚአብሔር ? ለእነዚህ ጥያ ቄዎች የተለያዩ መልሶች የሚሰጡ እንዳሉ አያጠያይቅም ።

አማንያን — ነቢያቶቹም ሆኑ ሐዋ ርያት በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ የጻ ፉት ነው ብለው ይቀበላሉ ያምናሉም። ተቃዋሚዎቹም በበኩላቸው የሌሎች ልዩ ልዩ የእምነት መጻሕፍትና ተራው ድርሰት ሁሉ በመንፈስ በተመሩ ሰዎች የተጻፉ ናቸው ብለው ይከራከ ራሉ ። ይሁን እንጂ ተቃዋሚዎችም ቢሆኑ የጌታችን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነቱን ሲጠራጠሩ በጣም ትሁት ፣ ርኅሩኅ ፣ ደግ ፣ እውነተኛም ሰው መሆኑን ያም ናሉ ይቀበሉታልም ። ከራሳችን ባ ሕርይ እንደምናውቀው ሁሉ እውነተ ኛ ሰው ክፉ ነገር አያደርግም በቃሉ ም ሐሰት አይገኝም ።

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ በብሉ ያት ክፍሉ ደግሞ ደጋግሞ እንዲህ ይላል « የሠራዊት ጌታ የእግዚአብ ሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ እሥራኤል ሆይ ስማ — አምላክህስ እኔ አምላክህ ነኝ ከእኔ በቀር ሌላ አም ላክ የሉም» እያለ የደኅንነትን መንገድ ይሰብካል ያውጃልም ። በፍልስፍና ወይም በሌሎች መጻሕፍት እንዲህ ዓይነት አቀራረብ አጻጻፍ ታይቶ ተሰ ምቶም አይታወቅም የለምም አይኖ ርምም ። በሐዲሳትም ጌታችን መድ ኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄ ዳለሁ» ዮሐ- ፲፮ ፳፰ መልሶ ደግሞ አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ» ዮሐ- ፲፭ ፭ ሲል እናገኘዋለን ። ታዲያ እውነተኛነቱ በኢአማንያንና በአማንያን ዘንድ የተ ረጋገጠው ክርስቶስ በነቢያቶቹ አድሮ እንዲያ ካናገረ ራሱም እንዲህ ከተና ገረ መጽሐፍ ቅዱስም የእርሱ ቃል የተመዘገበበት ማኅደር ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰት ነው እንላለን አንልም እውነት ነው እንጂ ። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ በግልጽ የሠራቸውን ታም ራቱን ትምህርቱን መዝገቦ ከመያዙም በላይ ለምድራዊ ዓለምም ሆነ ለሰማ ያዊው ዓለም የሕይወት መመሪያ ነው ሰው ሕይወቱን ለአንዲት ደቂቃ እን ኳን ብትሆን እጅግ አድርጎ እንደሚ ወዳት እናውቃለን ጣዕም አላትና እን ኪያ ልቅሶ ዋይታ ኃዘን መራብ መጠ ማት መታረዝ የሌለበትን ሕይወት ፍቅርን ሰላምን የምታድል ሕይወት ተቀምሳም ምንም ወደር የሌላትን ሕይወት ልንንከባከብ ያሻል ።

መጽሐፍ ቅዱስ በኢአማንያን ዘንድ ለቁጥር እስከሚያታክት ድረስ ተነቅ ፏል ተጥሏል ተወርውሯል መጻሕፍ ቱም እንዲገነጣጠሉ በእሳትም ው ስጥ እንዲጋዩ ተደርጓል ። እንዲህ ዓይ ነቱ በደል ቢደርስበትም ቅሉ የበደሉ ትንና ዘመናትን አሳልፎ ከእኛ ዘመን ደርሷል ሰው ገፍቶ ሊጥለው የማይ ችል ዓለት ነውና የሕይወት ቃል ነ ውና ። የሚያስገርመው ግን በዚህ መጽሐፍ ላይ የሚደርሰው ጉዳት በተ ባባሰበትና ፍጹም ጠፋ ተብሎ በሚ ታሰብበት ወቅት ከመቼውም በበለጠ ፍጥነት እያንዳንዱን አገር ከዳር እስ ከዳር እያዳረሰ እየማረከም ነው በዚ ህም ሕያውነቱን አረጋግጧል ።

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተቸትና ለመ ንቀፍ በየዘመኑ የተጻፉትን ጽሑፎች ሰብስበን በአንድነት ብንከምራቸው በዚህች ምድር ላይ እጅግ ከፍተኛ ከሆ ነው ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ልቆ እንደሚ ገኝ ከተቃዋሚዎቹ የሚጻፉት ትች ቶች ሁሉ እንዲያጠፉት የተሰነዘሩ ሲሆኑ ከአማኞችም ዘንድ ደግ የሠሩ እየመሰላቸው ቃሉን በማጣመም በሚ ያደርጉት ቅራኔ የፈጸሙት በደል ለመ መዝገብ እጅግ አዳጋች መሆኑን በታ ሪክ ማኅደር እንረዳለን ። ሰው በምር ምር የጻፋቸው የደረሳቸው መጻሕፍት ይህን ያህል እንግልት ሳይደርስባቸው ከሰው ሃሳብ የመነጩ በመሆናቸው ለታሪክ ያህል ተመዝግቦ ከመቀመጥ በስተቀር መሠረተ ሃሳባቸውን በየዘ መናቱ ሌሎች ሰዎች እያሻሻሏቸው ይገኛሉ ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከተቃ ዋሚዎቹም ሆነ ከአማኞቹ የሚሰነዘ ርበትን ተቃውሞ ተቋቁሞ ከሦስት ሺህ ዘመናት በላይ ምንም ሳይታከል በት ሳይቀነስለት ሳይለወጥ ጸንቶ መገ ኘቱ በእውነት የሕይወት ቃል በመ ሆኑ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ ወደእዚህ ዓለም የተላከልን ዘመናትን አሳልፎ ጸንቶ ለመኖር መሆኑን የተተረጎመባ ቸውን ቋንቋዎች ብዛት ብቻ በመመ ልከት ለመረዳት ይቻላል ። ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት ከሃያ ወይም ከሰ ላሣ በማያንሱ ቋንቋዎች ታትሞ ይገኝ የነበረው መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ በሃያ ኛው ክፍለ ዘመን በዚህ የምርምር ዘ መን በዚህ የረቀቀ ሥልጣኔ በተስፋፋ በት ዘመን ጥርጣሬም በነገሠበት ዘ መን ከሺህ በላይ በሆኑ ልዩ ልዩ ቋንቋ ዎች ተተርጉሞ ይገኛል ። የትም አገር ይሁን የትም በእርግጥ በብዙ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚገኝ መሆኑን ለማረጋገ ጥና ለመታዘብ የሚጓዙ ቢሆን ከእር ስዎ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ከዚያ ሥ ፍራ ቀድሞ ይጠብቅዎታል ። ቀሳው ስት ዲያቆናት አብያተ ክርስቲያናትና ሰባክያን ከሌሉበት አገር ከጥቂት ሰዓት ጉዞ በኋላ ለመድረስ ይቻላል መጽሐፍ ቅዱስ የሌለበት አገር ግን የለም ። ይህ አስገራሚ ሁኔታ ሊፈጠር



www.ethiopianorthodox.org

የቻለው ይህን መጽሐፍ የሚያጥላሉት ተቃዋሚዎች እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ካለበት ሥፍራ ፍቅር ሰላም የሚሰፍን መሆኑን ስለሚያውቁ በዚያ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥላ ሥር ለመጠለል ይሻሉ ።

በሌላ አንጻር ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በጠበብቶች የተጻፈና በመንፈሳውያን ኮሚቴ ሳንሱር (የተመረመረ) የተደረገ ቢሆን ይህንንም አንድ የሃይማኖት ድርጅት ወይም ማኅበር ያሳተመው ቢሆን ኖሮ የኖኅን ስካር የአብርሃምን ሽንገላ የሎጥን ውድቀት የያዕቆብን ማታለል የዳዊትን ሲሰኝነት የጳውሎስንና የባርናባስን ጠብና ጭቅጭቅ የጴጥሮስን ክህደት እናነብበውም ነበር ። ደራሲውም ኮሚቴውም ድርጅቱም እነዚህን ቅዱሳን ያቃለሉ መስሏቸው ታሪኩን ከመጽሐፉ ውስጥ የሰቀሩት ነበርና ። እውነተኛውን የማዛባቱን ጉዳይ ከታሪክ መጻሕፍት በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን ። የጦርና የአገር መሪዎች የኃያላንና የነገሥታትን ታሪክ መመልከቱ ብቻ በቂ ነው የእነዚህን ሰዎች ዜና ለማጋነን የሠሩትን ደግ ደጉን ብቻ መርጠው በማቅረብ ታሪክ ተጻፈ ተብሎ ራሱን የማታለሉ ጉዳይ በቂ አስረጅ ነውና ። የመንፈስ ቅዱስ የታሪክ አቀራረቡ እንዲህ አይደለም እቅጯዋንና እውነተኛዋን ታሪክ ብቻ እንጂ ስለዚህም ከሰው ዘር ማንም ቢሆን ታሪኩን እግዚአብሔር እንዲጽፍበት አይፈልግም ራሱን በራሱ ታዝቦታልና ማንነቱንም ያውቀዋልምና ። በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁላችንም በደለኞች መሆናችንንና በእምነታችንና በሥራችን የምንድን መሆናችንን ለመግለጽ ለማስተማር ለሕይወታችንም መመሪያ እንዲሆን እነዚህንና ሌሎችንም ታሪኮች መጽሐፍ ቅዱስ መዝግቦ ሰጥቶናል ።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል አይደለም እውነተኛም አይደለም ብሎ ለማስተባበልና ሐሰተኛም ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ሁሉ ከንቱ መሆኑን ከሚከተሉት ሁኔታዎች ለመረዳት እንሞክራለን። የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ጸጋውንና ክብሩን ተገፍፎ ወደእዚህ ዓለም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ሥጋዊው ኑሮውን ለማሻሻል ብዙ ጥረት ማድረጉና በማድረግም ላይ መሆኑን እናውቃለን ። ለእዚህም ይረዳው ዘንድ የሒሳብንና የፍልስፍና ጥበቡን የከርሠ ምድር ጥናቱን የከዋክብትንና የገጸ ምድር ዕውቀቱንና ሌሎችንም ጥበቦች ሁሉ በጣም ወደ ረቀቀ ደረጃ ያደረሰ ቢሆንም ቅሉ ሕሊናውንና የሰብእናውን ክብር የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል ያላሻሻሉለት ያላረኩለትም መሆኑን ከዕለት ተግባራችን መረዳት ይቻላል ። እንዲያውም ሰው ምድራዊ ሕይወቱን ለመንከባከብ በሚያደርገው ጥረት ሁሉ ሞራሉ እየወደቀ ክብሩን ለምድራዊ ተድላ እየለወጠ መሆኑን የእያንዳንዳችን ሕይወት በቂ ምስክር ነው። ይህም ሲባል «ሲሠራ የማይወድ አይብላ» የሚለውን የክርስትና ትምህርት «በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ » የሚለውንም መለኮታዊ ትዕዛዝም በመዘንጋት አይደለም ። ሰው በሕይወተ ሥጋው እስካለ ምግብ ልብስና መጠለያ ያስፈልጉታል ። እነዚህን ለማግኘትም መሥራት አለበትና ።

ከእዚህ ላይ የምንፈልገው ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሰነፎችና የደካሞች ማነብነቢያ ሳይሆን የጠንካሮች ፤ የልበ ሙሉዎች ፤ የአርቆ አስተዋዮች በቃሉ የታነጹ አማኞች ሠራተኞች መሣሪያ መሆኑንና ክርስቲያን በዕለት ኑሮውም ቢወድቅም ቢነሣም የጥበብና የዕውቀት መራቀቅ የኃያላንና የዘመናት ክንድ ሊያናውጹበት ባልቻሉትና በማይችሉት እምነት ተስፋ ፍቅር ጸንቶ ለመኖር አንድ መንገድ አንድ ይሕወት ፤ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ያውቃልና ። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» «ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም» በሚሉት ቃላት ገልጸውለታል አስተምሮታልም ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጸው ሰላም ክርስቶስ ነው ፍቅር ክርስቶስ ነው ሕይወትም ክርስቶስ ነው የሚል ነውና ።

እንግዳ ወርቅ ጥሩነህ
ዊ. ዘአልድ ቡክ እስታንድ

## ሐዋርያዊ ትእዛዝ

ከ፲፩ኛው ገጽ የዞረ ፤

ትንም ለድ[illegible] ወደ እናንተ የመጣ እንግዳ ( ባሕታዊ ) በእናንተ ዘንድ ተቀምጦ ለመኖር ቢፈልግ ባለሙያ ሆኖ እየሠራ ይብላ ። ሞያ ከሌለው ክርስቲያን (ባሕታዊ) ነኝ በማለቱ ብቻ ሥራውን ፈትቶ በእናንተ ዘንድ እንዳይቀመጥ መርምሩ ። እንዲሁም ለመሥራት ባይፈቅድ ክርስቶስን የንግድ ዕቃ ማድረጉ ነውና ይህን ከመሳሰሉ ሰዎች ተጠበቁ ። » በማለት የወንጌል መምህርነትና የክርስትና ሃይማኖት ሌሎችን ለመርዳት የሌሎችን ሕይወት ለማዳን የራስን ሕይወት እስከ መሠዋት መሥራትን የሚጠይቅ እንጂ ለራስ መገልገያና የግል ጥቅም መፈለጊያ አለመሆኑን ሐዋርያት ከክርስቶስ እንደተማሩ አስተምረዋል እንደ—ታዘዙም ትክክለኛውን ትእዛዝ አስተላልፈዋል ።

ራደ አስረስ



# ፍ ቅ ር

ፍቅር ተወዳዳሪ የሌለው የመንፈሳዊ ነገር ሁሉ መሠረትና ጣራ እንደ መሆኑ መጠን የመንግሥተ ሰማያትም በርና ቁልፍ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ፍቅር የሁሉ በላይ መሆኑን ሲያረጋግጥ «እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት » ዮሐ- ፲፭ - ፲፪ ብሏል ።

ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም የኃጢአት ዘርፎች የሆኑትንና ወደ ጨለማ የሚወስዱ ፲፭ ፈቃዳተ ሥጋ እንዴት ያሉ መሆናቸውን ካስረዳ በኋላ በዚህም አንጻር የሕይወት ብርሃን ወደሚጐርፍበትና ወደ ብርሃን የሚመሩና ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መኖራቸውን ይገልጻል ፱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የተባሉትም በዝርዝር ሲገለጹ ፤

ፍቅር ደስታ ሰላም
ትእግሥት ቸርነት በጎነት
እምነት የዋሃት ራስን መግዛት
ናቸው ገላ - ፭ ፡ ፳፪ ።

ከዚህ ላይ ዘጠኙ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ተብለው ከሚጠሩት አንዱና የመጀመሪያውን ተራ ቁጥር ይዞ የሚገኘው ፍቅር ነውና ፍቅር በሚለው እንጀምራለን አንዳንድ ምሑራን እንደ ገለጹት ከበጐ ሥራዎች ሁሉ የዋህነት ይበልጣል ከየዋህነትም ቅን አስተሳሰብ ይገኛል ከቅን አስተሳሰብም ፍቅር ይወለዳል ስለዚህ ሕፀፅ የሌለበት ፍጹም ሕግ ስለሆነ የጽድቅ ሥራዎች ሁሉ ማሠሪያ ነውና ከፍቅር የበለጠ መንፈሳዊ ሕግ የለም ይላሉ ።

የሰው ልጆች በሃይማኖት ጸንተው በመንፈሳዊ ሥራ ተወስነው ቢኖሩና ከዚህም አልፈው ተርፈው ያለውን ንብረታቸውን ለነዳያን እየሰጡና ለተቸገሩ ሁሉ እየመጸወቱ መላ ዘመናቸውን ቢያሳልፉ ነገር ግን ይህንን ተግባር እየፈጸሙ የሕግጋት ማሠሪያ የሆነውን ፍቅር ካልያዙ ጾምም ሆነ ምጽዋት ስግደትም ሆነ ጸሎት ሁሉም ከንቱ ነው ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ፍቅርን ካልያዙ ማንኛውም መንፈሳዊ ሐሳብም ሆነ ሥጋዊ ሐሳብ ፈጽሞ እንደ ማይሳካና ከንቱ መሆኑን ሲያብራራ የሚከተለውን ጽፎ እናገኛለን «ተራራዎችን እስካፈልስ ድረስ እምነት ( ሃይማኖት ) ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ ።

ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍልና ከዚህም በላይ ሥጋየን ለእሳት አሳልፌ ብሰጥ (በሰማዕትነት ) ብሞት ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም» ብሏል ፩ኛ ቆሮ· ፲፫፡፪-፫።

ሐዋርያው እንደገለጸው ሰላምን ካልያዙ ፍቅርንም ካልተከተሉ የሚፈጸም ጉዳይ አይኖርም ፍቅርን የያዘ ሰው ግን ሳይበላ የጠገበ ሳይጠጣ የረካና ሳይለብስም የሞቀ ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም ።

ምክንያቱም ፍቅርን የያዘ ሰው የሚያስጋ ጠላት የሚከራከር ባላጋራ ስለሌለው ሁልጊዜ በደስታ ተውጦ ነውና የሚኖረው ።

ፍቅር ካለ ዘንድ ጥቂት ነገር ለብዙ ሰዎች ይበቃል ለዚሁም አምስት እንጀራ ለአምስት ሺህ ሰዎች ምግብ ሆኖ እንደቀረበና ከእነዚህም ለአምስት ሺህ ከቀረቡት አምስት ዳቦዎች ውስጥ ጠግበው የተረፈው ቁርስራሽ ፲፪ መሶብ ሙሉ እንደ ተነሣ በማቴዎስ ወንጌል ፲፬ ፡ ፲፱—፳ በቂ መረጃ ነው ይህ ሁሉ ያለ ፍቅር የተደረገ አይደለምና ፍቅር ከሌለ ግን ስንኳንስ ጥቂቱ ነገር ለብዙ ሰዎች ሊበቃ ብዙ ቢኖርም ለጥቂቱ እንደማይበቃ የሚያጠራጥር አይደለም ። በጣዕመ ፍቅር ያልተቀመመና ሰላም ያልተቀላቀለበት ሃይማኖት ጣዕም የለውምና ።

ጠቢቡ ሰሎሞንም ይህንን ነገር አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል «ጥል ባለበት ዘንድ እርድ ከሞላበት ቤት ይልቅ በጸጥታ (በፍቅር) ደረቅ ቁራሽ ይሻላል» ብሏል ምሳ - ፲፯ ፡ ፩ ።

እንደሚታወቀው ፍቅር የተለያዩትን የሚያዋህድ የተራራቁትን የሚያቀራርብ የጥልን ግድግዳ አፍርሶ ሰላምን የሚያንጽ የሕይወት መሠረት ነው ። ሌላው ቀርቶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከሰማያዊ ዓለም ወደ ምድራዊ ዓለም ሊመጣ የቻለው ከፍቅሩ ጽናትና የሰውን ልጅ ከመውደዱ የተነሣ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ እንዲህ ሲሉ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስከመስጠት ድረስ ዓለሙን ወድዶታልና ዮሐ· ፫ - ፲፮

የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ዮሐንስ አፈ ወርቅም የወንጌሉን ቃል በመከተል



www.ethiopianorthodox.org

( «ፍቅር ስሐቦ ለወልድ ኃያል እመ
ንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት») ፍቅር
የአምላክን ልጅ ከዙፋኑ ሳበው እስከ
ሞትም ድረስ አደረሰው ሲል በሰፊው
ጽፏል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ
ቁጥር ፶፫ በዓለም ውስጥ ብዙ ጥበባት
አሉ ነገር ግን በዓለም ከሚገኙ ጥበ
ቦች ከፍቅር ጋር የሚስተካከል ጥበብ
አይገኝም ።

ይህንን የፍቅርን ከፍተኛነት የተ
ገነዘቡ አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቅም ሲገ
ልጹ «ፍቅር መያዣ የሌለውን የሰውን
ልብ አሥሮ ለመሳብ የሚያገለግል የሰ
ላም ገመድ ነው ብለዋል ሊ.መ.ሞ.ዕ.

ይህ ብቻ አይደለም ሐዋርያው ቅዱስ
ጴጥሮስም በፍቅር ስለሚገኘው ታላቅ
ጸጋና መንፈሳዊ ኃይል ሲገልጽ እንግ
ዲህ እንደባለ አእምሮ አስቡ ትጸል
ዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ ካለ በኋላ
ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና
(ያጠፋልና) ይላል ፩ኛ ጴጥ. ፬ ፣ ፯ ።

እንግዲህ የፍቅር ምልክት በልቡ
ያልተሳለበትና የፍቅርን ጣዕም ያል
ቀመሰ ሰው ይልቁንም በክርስቶስ ክር
ስቲያን የተሰኘ ክርስቲያን ከሚፈለግ
በት ክርስቲያናዊ ተግባር ቅድሚያን
መያዝ ያለበት ፍቅርን ነው ፍቅር ከተ
ያዘ ሁሉም በሁሉ አለ መንፈሳውያን
ተብለው ከሚጠሩና የታቀደውን መን
ፈሳዊ እቅድንም ግቡን እንዲመታ
የሚያደርግ ፍቅር ነውና ።

በተለይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ
ስለ ፍቅር ያለውን የጋለ መንፈስ ሲያ
ብራራ «በዚህ ዓለም ጸንተው የሚኖ
ሩት ሃይማኖት ተስፋ ፍቅር ናቸው
ይልና እነዚህን ሦስት ቃላት ከጠቀ
ሰም በኋላ (ወእምኵሉ የአቢ ተፋቅሮ)
ከሦስቱ ግን ፍቅር ይበልጣል ብሏል
፩ኛ ቆሮ - ፲፫ ፣ ፲፫ ።

በዚህ ባለንበት ዓለምም የፍቅር ዓይ
ነት ብዙ ነው እንዲህ ሲባል ፍቅረ
እግዚአብሔር ፍቅረ ቢጽ ፍቅረ ሥጋ
አሉ ማለት ነው ።

እርግጥ ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ
ቢጽ ይመስላል ምክንያቱም እኔ እንደ
ወደድኋችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋ
ደዱ ዘንድ ነው በሚለው ቃል የተመ
ሠረተ ነውና እንዲህም ከሆነ የክርስ
ቶስ ተከታዮች ሁሉ በፍቅር ገመድ
ተሳስረው እርስ በእርሳቸው በመንፈ
ሳዊ ተግባር መጠያየቅ መተዛዘንና
መረዳዳት ይኖርባቸዋል ቅዱስ ጳው
ሎስም ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ መል
ካም እናድርግ በጊዜው ጊዜ እናጭዳ
ለንና መልካምን ሥራ ከመሥራት
አንታክት ሲል የተናገረውን ቃል
በተግባር መጠቀም ያስፈልጋቸዋል።
ገላ - ፮ ፣ ፱—፲ ።

ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም ተብሎ
ተጽፋልና ።

ክነፈ ርግብ ማርቆስ

# ክርስቲያኖች የትንሣኤን…

ከ፲፩ኛው ገጽ የዞረ

መመኪያ የእምነታቸውም ዋናው
መታወቂያ የክርስቶስ መነሣት ስለ
ሆነ ፤ አንድነታቸውም በዚህ ታላቅ
የክርስትና በዓል እንደተመሠረተ ሐቅ
ነው።ይህንም የተገነዘቡ የቀደሙ አባ
ቶች በቀኖና የወሰኑት በሥርዓትና በት
ምህርት ያጸኑት ለከንቱ አይደለም ።

ግን ይህ እንደ እገሌ አቆጣጠር የሚ
ለው ከስሕተት ያልዳነ ቀመር መጣና
የነ እገሌ የትንሣኤ በዓል የነእገሌ የል
ደት በዓል የሚባለው ምእመናንን ግራ
ሲያጋባ ማየቱ እንደ ቀላል ነገር መቆ
ጠር የለበትም ።

የተባበሩት መንግሥታት ማኅበ
ርም የካሌንደር ጉዳይ የሕዝብ ችግር
መሆኑን ተረድቶ እ/ኤ/አ/ ከ፲፱፻፷፫
ዓ·ም ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት
በፊት ጀምሮ ሰፊ ጥናት አድርጓል ።
በተለይም የኤኮኖሚውና የኅብረተ
ሰቡ ጉዳይ ክፍል በሕንድ የቁጥር ሊቃ
ውንት በኩል የጸደቀውን ጥናት እው
ቆት እ/ኤ/አ/ በ፲፱፻፴፱ ዓ·ም ተቀብ
ሎታል ። ከዚያም ወዲህ ሁሉም በየበ
ኩላቸው የተስተካከለ ከስህተት ነፃ
የሆነ የቀን መቁጠሪያ ለማዘጋጀት
ሊቃውንት መርጠው በመታገል ላይ
ናቸው ምናልባት ኮምፒውተር የተባ
ለው የተራቀቀ የሂሳብ መሣሪያ ይህን
ችግር በተሻለ መልክ ሊያቃልል ይ
ችል ይሆናል ። እስከዚያው ግን
እንደ አብዛኞቹ ጥንታውያን አብያተ
ክርስቲያናት የጥንቱን ሥርዓትና ውግ
ዘት አክብሮ በዓሉን አንድነት ማክ
በሩ መልካም ነበር ።

ያም ሆነ ይህ ለምን ክርስቲያኖች
የትንሣኤን በዓል በተለያዩ ዕለታት
ያከብራሉ ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ
በመጠኑ ከዚህ በላይ የተጻፈው ነው
ለምእምናን ተፈላጊው ነገር በዓሉ
ከበዓላት ሁሉ የበላይ መሆኑን አምኖ
ትንሣኤ ሙታንን እየተገነዘቡ በአም
ነት ማክበሩ ነው ።

«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት
በኩራት ሆኖ ተነስቷል ሞት በሰው
በኩል ስለመጣ ፤ ትንሣኤ ሙታንም
በሰው በኩል ሆኗልና ።» ፩ኛ (ቆሮ
ም ፣ ፲፭ ቁ- ፳—፳፩) ።



# ዜና ሊቃውንት

አለቃ ለማ ኃይሉ

የትውልድ ሀገራቸው በወሎ ክፍለ
ሀገር መቄት አቡነ አሮን የሆነው
አለቃ ለማ ኃይሉ ከአባታቸው ኃይሉ
ለውጤና ከእናታቸው ወይዘሮ ታሪክ
አጥቌ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግ
ሥት መጨረሻ አካባቢ ተወለዱ ።

በትውልድ አገራቸው የመጀመሪያ
ውን ደረጃ የንባብ ትምህርት ተከታ
ትለው ዳዊት ከደገሙና በዜማም በ
ኩል ጾመ ድጓንና ምዕራፍን ከተማሩ
በኋላ ከአንዱ ወደሌላው የዜማ ባለ
ሞያ በመዘዋወር ፀዋትወ ዜማዎችን
በሚገባ ተምረው አጠናቅቀዋል፤ በዚ
ሁም ወቅት ግብፃዊ ከነበሩት ጳጳስ
ከብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ መዓርገ ዲቁ
ናን ተቀብለዋል ።

አለቃ ለማ ኃይሉ ምንም እንኳ የዲ
ቁና ሥልጣን በልጅነት ዕድሜያቸው
ቢቀበሉ የትምህርት ጊዜያቸው እንዳ
ይጣበብባቸውና የልዩ ልዩ ምሥጢር
ምርምር እንዳይገታባቸው በግብረ
ዲቁናው ተልዕኮ ለረጅም ጊዜ አልሠ
ሩበትም ።

በመሆኑም እየላ ሚካኤል በመባል
ወደታወቀው ደብር ተዛውረው በቅኔ
ፈጣሪነታቸው ከታወቁትና እጅግ አድ
ርገው ከተደነቁት ከመሪጌታ ቀጸላ
ዘንድ ቅኔ ከነአግባቡ ተምረዋል፤ የዋ
ድላን የቅኔ ፈጠራ ስልትና የአገባብ
መንገድ ለማጠናከርና ተምሮ ለማስተ
ማር በነበራቸው ፍላጐት ወደዋድላ
ሔደው«ጨሐፋንታ» ከተባሉት ሊቅ
የቅኔ ሞያቸውን በሚገባ አጥንተው
አደላድለው ለመምህርነት ተመርቀ
ዋል ።

ሊቁ የቅኔ ምርምርና የመንገዱ ቅ
ያስ ወይም አቅጣጫ እንደየቤቱ ልዩ
ነትን የሚያሳይ መሆኑን በጥልቅ ሁ
ኔታ ስለገመገሙ ከላይ በተመለከቱት
በሁለቱ የቅኔ ባለሙያዎች መምህራን
ብቻ የቅኔ ክትትል ሒደታቸውን አል
ገቱም ፤ በመሆኑም በአማራ ሳይንት
ውስጥ ሠገራ ጊዮርጊስ ተብሎ ከሚ
ጠራው ደብር ይገኙ ከነበሩት ሊቅ
ከመምህር ወልደ ኪሮስ ፤ በጐጃም
ክፍለ ሀገር ከዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ደብር ከመምህር ተጠምቆ የቅኔ ትም
ህርት ሞያቸውን በይበልጥ አስፋፍ
ተው የሁሉንም የቅኔ መንገድና ስልት
ተከታትለው አውቀው የፈለጉትን
የቅኔ ፈሊግ በማስመልመከት ለመቀ
ኘትም ሆነ ለማስተማር የተሟላ
ችሎታ አግኝተዋል ።

ከዜማና ከቅኔ ትምህርታቸውም
በኋላ ለመጻሕፍት ትርጓሜ ጥናትና
አካሔድ ተከታታይ ትኩረት ስለሰ
ጡት ከመጨረሻው የቅኔ መምህራ
ቸው ከመምህር ተጠምቆ ዘንድ በጠ
ቅላላው የመጻሕፍተ ብሉያትን ትር
ጓሜ በሚገባ ተምረው አውቀዋል ።

ዓፄ ዮሐንስ የጐጃምን ክፍለ ሀገር
በጦር ኃይል በመቱበት ወቅትም ዓይነ
ሥውሩን መምህራቸውን መምህር
ተጠምቆን እየመሩና እየረዱ ከጐጃም
ወደሸዋ ክፍለ ሀገር መጥተዋል ።

በዚህም ጊዜ ከብሉያት ጉባኤ ወደ
መጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ ተመል
ሰው በሐረር ክፍለ ሀገር የአሰቦት
ገዳም አስተዳዳሪ ከነበሩትና በሊቅነ
ታቸው በጣም ስመ ጥሩ ከነበሩት ከአ
ለቃ ገብረ መድኅን የመጻሕፍተ ሐዲ
ሳትንና የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ
አደላድለው አውቀዋል ። በተጨማ
ሪም በደብረ በግዕ ከመምህር ወልደ
ማርያም ፤ እንዲሁም ዓፄ ምኒልክ የፍ
ርድ አደባባይ ፍትሐ ነገሥት አው
ጭና ተርጓሚ ከነበሩት ከታላቁ ስመ
ጥር ሊቅ ከመልአከ ብርሃን ወልደ
ዮሐንስ ፤ የቄርሎስንና የዮሐንስ አፈ
ወርቅን ትርጓሜ አጣርተው ተምረ
ዋል በአጠቃላይ የቅኔ ፤ የብሉይ ፤ የሐ
ዲስ፤የሊቅ ትርጓሜ መምህርና የኢት
ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ
ቲያን ከፍተኛ ሊቅ ለመሆን ችለዋል።

የሊቁ ከፍተኛ ችሎታ እየጐላና
በሁሉ ዘንድ እየታወቀ እንደመሔዱ
መጠንም በቅድሚያ የአዲስ አበባ
ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቀጥሎም
የሐረር አደሬ ጢቆ ሥላሴ አድባራት
አስተዳዳሪነት በየተራ ተሰጧቸው
በማስተማርም ሆነ በማስተዳደር ለኢ
ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ
ክርስቲያን አስተዋፅኦ አበርክተዋል ።

በታሪክ ፤ ልዩ ልዩ ኢትዮጵያዊ ባህ
ልና ምሥጢረ መጻሕፍት ረገድ ሊቁ
ለሚቀርብላቸው ጥያቄ የሚሰጡት
መልስ በቂና አጥጋቢ በመሆኑ የምር
ምር ሰዎችና ታሪክ አጠናቃሪዎች በ
ሞት በመታጣታቸው የተሰማቸውን
ኃዘን በማያቋርጥ ድምፅ ያስተጋቡ
ታል ።

አንዳንድ ጊዜ እንዲሁ ሳይጠየቁ
ስለቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ ነገሥታ
ትና በየዘመናቸው ስለነበሩት የኢት
ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እን
ዲሁም ስለሃይማኖት ስልት በየረድፉ
የሚያደርጉት ጥንታዊና ወቅታዊ ትን
ታኔ እጅግ አድርጐ የሚያመረቃና
የሚያጠግብ ነበር ።

የሕይወት ዘመናቸውም ሩቅ ባለ
መሆኑ በዚህ ጽሑፍ ላይ ስላሰፈርነው
ሁኔታ የጆሮም ሆነ የዓይን ምስክሮች
በብዛት ለማቅረብ ይቻላል ።

ከላይ ከተጠቀሰውም ሌላ መንፈስ
እግዚአብሔር ያደረባቸው ስለሆኑ
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተናገሩዋ
ቸው የትንቢት ቃላት ጊዜያቸውን
እየጠበቁ በሥራ ተተርጉመዋል ይኸን
ኑም ዝርዝር ሁኔታውን የነገሩዋቸውና
የዕድሜም ዕድል አግኝተው ትንቢታ
ቸው ሲፈጸምና በሥራ ሲተረጐም
ያዩት ሁሉ ያደንቋቸዋል ።

ይሁን እንጂ ከቃለ—ትንቢታቸው
የሚታወቀውን እንኳ ለመግለጽ አስፈ
ላጊ መስሎ ስላልታየ አልፈነዋል ።

ሊቁ ሲማሩ የተማሩትን ሲያስተ
ምሩ የተጠየቁትንም ሆነ ያልተጠየቁ
ትን ጠቃሚ ትምህርት ሁሉ ያለማመ
ንታትና ያለችግር በሙሉ ድምፃቸው
ሲያስረዱ ኖረው ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፶፱
ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው
መንፈሳዊ አገልግሎት ከማበርከት
ጋር ባቀኑትና ባጸኑት በመንበረ ፀባ
ዖት ቅድስት ሥላሴ ደብር ሥርዓተ
ቀብራቸው ተፈጽሟል ።

ከፍ ብሎ እንደተዘረዘረው በቅኔ
ሞያቸው የታወቁት ሊቁ አለቃ ለማ
ኃይሉ በየክብረ በዓላቱ በታላላቅ አድ
ባራትና ገዳማት እጅግ የሚደነቁ ቅኔ
ዎችን አበርክተዋል ። ከብዙዎቹ መካ

ተከታዩ ወደ፳፪ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ግዕዝ የግዕዝ ትምህርት

## ትምህርት ፲፩

**ሥርዓተ ተናብቦ** — **የተናባቢ ሥርዓት**

**መከሥት** — **መግለጫ**

ባለፈው የግእዝ ቋንቋ ጥናታችን መድረሻ ፊደላቸው ሣልስ የሆኑ ስሞች እንዴት እንደሚናበቡ ተምረናል ።
ለማስታወስ ያህል ከሣቲ ገላጭ ብርሃን ብርሃን ሲናበቡ «ከሣቴ ብርሃን» በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ሁለተኛው
ንና ሦስተኛውን ሥርዐተ ተናብቦ እንማራለን ።

በቅድሚያ መድረሻ ፊደላቸው ሳድስ የሆኑ ስሞችን እንጻፍ

| ቃላት | | | |
|---|---|---|---|
| መሠረት | መሠረት | ዐርከ | ወዳጅ |
| ዐረፍት | ግድግዳ | ሀሊብ | ወተት |
| ጥኅት | ደጃፍ | ሕልቀት | ቀለበት |
| መዝራዕት | ጡንቻ | ማዕጸድ | ማጭድ |
| አጽባዕት | ጣት | አሣዕን | ጥንድ ጫማ |

**መከሥት** ከዚህ በላይ የጻፍናቸው ቃላት ከሌላ ቃል ጋር ሲናበቡ መድረሻ ፊደላቸው ወደ ግእዝ ይለወጣል ።

**ምሳሌ ፦**

| | |
|---|---|
| መሠረተ ቤት | የቤት መሠረት |
| ጥኅተ ቤት | የቤት ደጃፍ |
| መዝራዕተ እድ | የእጅ ጡንቻ |
| አጽባዕተ እድ (እግር) | የእጅ (የእግር) ጣት |
| ሀሊበ ላህም | የላም ወተት |
| ሕልቀተ ወርቅ | የወርቅ ቀለበት |
| ማዕጸደ ሥርናይ | የሥንዴ ማጭድ |
| አሣዕነ ማእሰ | የቆዳ ጫማ |

ቀ ስተኛውን ሥርዓተ ተናብቦ እንመልከት

**መከሥት** መድረሻ ፊደላቸው ራብዕ ሐምስና ሳብዕ የሆኑ ስሞች ሁሉ ሳይለወጡ ከሌላ ቃል ጋር ይናበባሉ ።

**በቅድሚያ** ግን ቃላትን እንጻፍ

| ራብዕ | | ሐምስ | | ሳብዕ | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዜና | ወሬ | ህላዌ | ኑሮ | ውጽቦ | ቀለበት |
| ዜና | ሽታ | ሱታፌ | አንድነት | መርሆ | መክፈቻ |
| ሐተታ | ምርመራ | ጽዋኤ | ጥሪ | መሰንቆ | ማሲንቆ |
| ዜዋ | ምርኮ | ይባቤ | እልልታ | | |

አሁን ከሌላ ቃል ጋር አንድ ፊደል ሳይለውጡ እንዴት እንደሚናበቡ እናስተውል ።

| | |
|---|---|
| ዜና ዐለም | የዓለም ወሬ |
| ሐተታ ነገር | የነገር ሐተታ |
| ዜዋ ሕዝብ | የሕዝብ ምርኮ |
| ህላዌ ሰብእ | የሰው ኑሮ |
| ሱታፌ ሀገር | የሀገር አንድነት |
| ጽዋኤ ከብካብ | የሠርግ ጥሪ |
| ይባቤ ደናግል | የልጃገረዶች እልልታ |
| ውጽቦ ወርቅ | የወርቅ ቀለበት |
| መርሆ መዛግብት | የሣጥኖች መክፈቻ |
| መሰንቆ ማኅሌት | የዘፈን መሰንቆ |



# በጅማ ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት ከፍተኛ ስብሰባ ተደርጓል

በአዲስ አበባ ከተማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠ/ ጽ/ ቤት ከግንቦት ፴ እስከ ሰኔ ፮ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ-ም የተደረገውን ታሪካዊ የሆነ የሰበካ ጉባኤ ማደራጃና ማጠናከሪያ ሰሚናር ተግባራዊ ለማድረግ በከፋ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በመርሐ ጽድቅ ስብከተ ወንጌል አዳራሽ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ-ም ከፍተኛ ስብሰባ ተደርጓል ።

በዚሁ ስብሰባ ላይ ብፁዕ አቡነ ኤልሣዕ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፣ መምህር ገ/ማርያም ተስፋ ሥላሴ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ሠራተኞችና በጅማ ርዕሰ ከተማ የአውራጃ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ አባላት የአምስቱ አድባራት አለቆችና አገልጋይ ካህናት ፣ የየአድባራቱ አጥቢያ ሰበካ ጉባኤ ተመራጮች የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች የስብሰባው ተካፋይ ሆነዋል ።

በተደረገው ስብሰባ ብፁዕ አቡነ ኤልሣዕ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ስብሰባውን በጸሎት በከፈቱበት ወቅት የሰበካ ጉባኤን ማደራጃና ማጠናከሪያ ጉዳይን አስመልክተው ባደረጉት አጭር ንግግር ከግንቦት ፴ ቀን እስከ ሰኔ ፮ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ-ም በአዲስ አበባ መንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት የተደረገውን አገር አቀፍ ሰሚናር ጠቅሰው በከፍተኛ ደረጃ የተካሔደው ብዙ ድካም የተከፈለበት ሲሆን በጉባኤው መጨረሻ የወጣው የጋራ መግለጫ እጅግ የሚያስደስት መሆኑን ገልጸዋል ።

በዚህ በታሪካዊው ሰሚናር መክፈቻ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ተገኝተው የሰጡት አባታዊ መሪ ቃልና ትምህርት ለስብሰባው ጠቃሚ መሆኑን ካስረዱ በኋላ ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ከጉባኤው መክፈቻ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ በሊቀ መንበርነት በመምራት ለሰሚናሩ መሳካት ያደረጉት ጥረትና ድካም ፣ ትዕግሥት የተሞላበት አመራር ስለሆነ የጉባኤውን ተካፋይ እጅግ ያስደሰተ መሆኑን ገልጸው ለቤተክርስቲያን እድገት ለሰበካ ጉባኤ መደራጀትና መጠናከር ቆርጠው የተነሱ መሆናቸውን አድንቀው የዛሬው ስብሰባ ተካፋይ የሆናችሁ የቤተክርስቲያን አባላት በሙሉ ይህ ከፍተኛ መሥዋዕት የተከፈለበት ሰሚናር ያወጣው መመሪያ ማዕከላዊነት ተጠብቆ ተግባራዊ እንዲሆን አደራ ተጥሎባችኋል በማለት ካስገነዘቡ በኋላ አያይዘው እስከ ዛሬ ድረስ ለቤተክርስቲያናችን እድገት እንቅፋት ለሰበካ ጉባኤ መዳከም ምክንያት ሆኖ የቆየው ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው የሚያወጣቸው ቃለ አዋዲና የሚተላለፈው የቤተ ክርስቲያን መመሪያ በሥራ ላይ ባለመዋሉ ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል ቀጥሎም ከአሁን በኋላ ግን እያንዳንዳችን ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጠን የመነሳት ኃላፊነት አለብን ሲሉ ተናግረዋል ።

ከብፁዕነታቸው ንግግር ቀደም ብሎ መምህር ገብረ ማርያም ተስፋ ሥላሴ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መግለጫ ሰጥተዋል ። በዚህ ባቀረቡት መግለጫ ፣

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በ፲፱፻፸፫ ዓ-ም ስለሰበካ ጉባኤ መደራጀትና መጠናከር ያወጣው መመሪያ አብዛኛውን ተግባራዊ ባለመሆኑ ያስከተለውን ችግር ጠቁመው መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው በቅድሚያ በሀገረ ስብከቱ የሚገኙ ካህናትና ከአብያተ ክርስቲያን የተመረጡት የሰበካ ጉባኤ ተመራጮችን አሰባስቦ የማስተባበር ፣ የማስተማርና የማደራጀት አስፈላጊነትን ገልጸው የአገር አቀፍ ሰሚናር በጠቅላይ ቤተ ክህነት ለሰባት ቀናት በተካሔደው ሰሚናር ብዙ ጠቃሚ ትምህርት የተሰጠ መሆኑን አስረድተዋል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክስርቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት አባል ከመሆኗም በላይ የአፍሪካ ጥንታዊት ቤተክርስቲያን መሆኗን ታሪክ ያረጋግጣል ብለው ምሳሌ ሲጠቅሱ በኢትዮጵያ ሥልጣኔ እንዲፈነጥቅ ፣ በባሕል ፣ በሥነ ጽሑፍ ፣ በትምህርት ዕውቀትና በልዩ ልዩ ሥፍራዎች እንደ አጥቢያ ኮከብ እያበራች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለትውልድ እያስተላለፈች የኖረችና የምትኖር ናት በማለት አያይዘው ገልጸዋል ። እንዲሁም አሥራ ስምንት ሚሊዮን ምዕመናን ፣ አያሌ ካህናት ፣ በርካት ያሉ አብያተ ክርስቲ



www.ethiopianorthodox.org

ያናት ያሏት መሆኗን የታሪክ መዝገብ ያስረዳል ።

ስለዚህ የታሪክ ባለቤት የሆነችውን ቤተክርስቲያን በቅዱስ መንፈስ ፤ በእኩልነት የሚመሩና የሚያስተዳድሩ የሰበካ ጉባኤ አባላት ከእሷት በዙሪያዋ ጨለማ ፈጽሞ አይኖሩባትም ። በአሁኑ ጊዜ ከመቼውም የበለጠ ትኩረትና ቅድሚያ የተሰጠው ለሰበካ ጉባኤ ማደራጀትና ማጠናከር ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ካስተማረው ትምህርት ጠቅሰው ሲያስረዱ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ»በማለት የምዕመናን ጥበቃ ከፍተኛ ኃላፊነት መሆኑን አስገንዝበው ስለበጉቹ ማለት ስለምዕመናን በመስቀል ለሞት ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ ሁሉ እኛም በአለን ኃላፊነት መሥዋዕትነት ከፍለን በተላለፈው ቃለ ዓዋዲና መመሪያ መሠረት ሰበካ ጉባኤን ማደራጀትና ማጠናከር አለብን ብለዋል ።

እንዲሁም ስለሰበካ ጉባኤ ከወረዳ እስከ ጠ/ቤተክህነት ሰበካ ጉባኤ መምሪያ የተዘረጋውንና የሚዘረጋውን የጠበቀ ግንኙነት የሰሚናሩ ተካፋይ ሆነው የተመለሱት አባላት ያለባቸውን ኃላፊነት ካስጠነቀቁ በኋላ የሰበካ ጉባኤ መጠናከር በችግር ምክንያት የተዘጉትን አብያተ ክርስቲያናት እንዲከፈቱ ምዕመናን መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንዲያረኩና ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፉ የሚረዳ መሆኑን አስረድተው ለዚህ ታላቅ መንፈሳዊ ጉባኤ ውይይት መክፈቻ በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ስም አቅርበአለሁ ካሉ በኋላ ብፁዕነታቸው ይህን ጉባኤ በጸሎት ከፍተው መንፈሳዊ ትምህርት እንዲሰጡ በጉባኤው ስም ጠይቀዋል ።

ከብፁዕነታቸው ንግግር ቀጥሎ የሀገረ ስብከቱ የሂሣብ ሹም አቶ ለማ ታደሰ ስለገቢና ወጭ ገንዘብ አያያዝ ሕጋዊ መንገድ እንዲኖር በአንድ አይነት ካርኒ እንዲሠራ ካስረዱ በኋላ በወጣው መርሐ ግብር መሠረት የሰሚናሩ ተካፋይ ሆነው ከተመለሱት አባላት ውስጥ ፩ኛው በስብሰባው ላይ ከወረዳ እስከ ጠ/ቤተ ክህነት ያለውን የሥራ ግንኙነትና የሥራ ዘርፍ በየደረጃው አስረድተዋል ።

ቀጥሎም አባ በለጠ ቹሩ ስለሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ያለባቸውን ኃላፊነትና ከሰበካ ጉባኤ ጋር ያላቸውን የሥራ ድርሻ በዝርዝር ገልጸዋል ።

እንዲሁም አባ በላይ እጅጉ ስለስብከተ ወንጌል መስፋፋትና በአሁኑ ጊዜ የሰባኪያን እጥረትና ያስከተለውን ችግር አስመልክተው ሰፋ ያለ ንግግር ካደረጉ በኋላ ይህ ችግር ሊፈታ የሚችለው ሰበካ ጉባኤ ተጠናክሮ በያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ካሉት ካህናት መካከል የስብከት ዝንባሌ ያላቸውን ካህናት መርጦ ማስልጠን አማራጭ የሌለው መሆኑን አስረድተዋል ።

መምሬ መንክር አስፋውም በበኩላቸው ስለጥንታዊ ቅርሳ ቅርስ ሁኔታ ባደረጉት ንግግር የቤተክርስቲያን ንብረት የሆኑ ታሪካዊ ዕቃዎች መካከል በአፄ ናዖድ ስም የሚጠሩ ታላላቅ መጻሕፍት ያለበትን አካባቢ ጭምር ለጉባኤው ገልጸው እነዚህ ታሪካዊ የሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅርስ የሆኑ ዕቃዎች እንዳይበላሹ ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው የሚጠበቁበት ውይይት እንዲደረግ አጥብቀው አሳስበዋል ።

ከዚህ ገለጻ በኋላ ለጉባኤው በያንዳንዱ ጉዳይ ጥያቄ ቀርቦ የሚመለከተው ክፍል መልስ ሰጥቶ ካበቃ በኋላ በዕለቱ ስብሰባ የተገኙት የሰበካ ጉባኤ አባላት የየደብሩ አስተዳዳሪዎች ካህናትና መዘምራን በአዲስ አበባ የተካሔደውን ታሪካዊ ሰሚናር በማድነቅ ተግባራዊ ለማድረግ ቃል ገብተዋል።

ከዚህም ሌላ ቀደም ሲል በጅማ ርዕሰ ከተማ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ተቋቁሞ በአንዳንድ ምክንያት ተቋርጦ እያሌ ወራቶች የቆየውን መምህር ገ/ማርያም ተስፋ ሥላሴ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ከነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ጀምሮ በተከታታይ ስብሰባ አድርገው በመካከሉ የተፈጠረውንና የአጠቃላዩ ሰበካ ጉባኤ ሥራ ያቋረጠበትን ችግር ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት አድርገው አባላትን አሰባስበው ውይይት ከተደረገ በኋላ ለወደፊቱ አዲስ ምርጫ ተካሒዶ እስከተተካ ድረስ የቀድሞው ተመራጮች ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ከማድረጋቸውም በላይ ከሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ውስጥ ለአጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ አንድ ክፍል ቢሮ ከነሙሉ ድርጅት አስረክበዋል ። በዚህ መሠረት በአሁኑ ጊዜ ሰበካ ጉባኤን ማጠናከርና ማደራጀት ከመቸውም የበለጠ እየተፋፋመ ሲሆን በሌላ በኩል የሰበካ ጉባኤ አደራጆችን በጅማ አውራጃ በስምንቱ ወረዳዎች አሰማርተዋል ።

---

## ዜና ሊቃውንት

ከ፳፩ኛው ገጽ የዞረ

ከል የታላቁን የመድኃኒታችንን የልደት በዓል አስመልክተው የተቀኙት ዋዜማ ቅኔ ከዚህ ቀጥሎ ተመልክቷል።

ኢይበቍዕ ክብረ አዝማድ ፤ እስመ ወልደ ባዕል ወድቀ በእደ ረኃብ ኃይል። አግብርት እንዘ ጽጉባን ወይተርፍ እክል ። ምሳሌ ዝኒ ነገር አጠየቀተነ ኀል ፤ እምጣነ ወልዳ ኢድኅነ እምለቢስ ቈዕል ። እንዘ ወርቀ ትፈትል ድንግል ።

(አማርኛው) አገልጋዮች ሲጠግቡና እህል ሲተርፍ የባለፀጋው ልጅ ኃይለኛ በሆነው በረኃብ እጅ ወድቋልና የዘመዶች ክብር አይጠቅምም ።

ድንግል ወርቅን ስትፈትል ልጅዋ ቅጠል ከመልበስ አልዳነምና የዚህንም ምሳሌ የከብቶች በረት አስረድታናለች » ።

ከሊቀ ዓምደ ጽዮን ተሰማ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት [illegible] አገልግሎት

ስልክ ቁ. 116616
የመል. ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org